# መልአኩ ወደ እኔ የመጣበት ምክንያት፡ እና ተልዕኮው

በርካታ የቴፕ መቅጃዎች ይታዩኛል... ወንድሞች፡ ይሄኛውም እንደሚቀዱት ግልጽ ነው። መንፈስ ቅዱስ የተናገራችሁ ነገር ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ የቴፕ መቅረጫዎች የያዙትን ወንድሞች በማንኛውም ጊዜ ጠይቁ፡ ያጫውቱላቸዋል፡ መልዕክታችሁ በትክክል መረዳት ትችላላችሁ። ልክ እንደተነገረላችሁ ካልተፈጸመ፡ ጠብቁ። ስለ አንድ ነገር "**ጌታ ሰራዊት እንዲህ ይላል**፡ 'ወይም **እንዲህ** እና **እንዲያ** ይሆናል'" ሲባል ሰምታችሁ፡ እንደተነገረ ካልተፈጸመ መርምሩት። አያችሁ? ሁሌም እንዲህ ነው።

2 አዎን፡ ትንሽ ገጽታ ለማስቀመጥ ያክል ነው... ሌላው እዚህ ስለተገኘነው ጥቂት ሰዎች እጅግ ደስተኛ ነኝ። የአንድ አገር ልጆች ነን፡ አይደለንም'ዴ? ማናችንም፡ ብንሆን፡ እንግዳማቾች አይደለንም። አይደለንም... ቤት እንዳለሁ እንዲሰማኝ የኬንታኪ ሰዋሰው መጠቀም እችላለሁ፡ ምክንያቱ እኛ'ኮ—እኛ'ኮ... ምናልባት ግን ከኬንታኪ የመጣ ሰው ካለ፡ ኬንታኪን ማጣጣሌ አይደለም። ከኬንታኪ የመጣ ሰው አለ'ዴ? እጅህን አንሳ። ቤት ውስጥ እንዳለ ሊሰማው ይገባዋል፡ በሉ'ጂ! አይገባኝም'ዴ? በጣም ጥሩ።

3 እናቴ የእንግዶች ማረፍያ ታስተዳድር ነበር። እና አንድ ቀን ለማየት ሄድኩኚ... ረዥም ትልቅ ጠረጴዛ፡ ተዘጋጅቶበታል፡ በዚያም እንግዶች ነበሩ። "ከኬንታኪ የመጣችሁ ስንቶች አላችሁ፡ እስኪ ቁሙ፡" አልኳቸው። ሁሉም ተነሡ። የዛኑ ቀን ማታ ቤተ ክርስትያን፡ ወደ ቤተ ክርስትያናችን ሄድኩ፡ እና ጠየቅኳቸው፡ "ከኬንታኪ ስንት ሰው መጣ? " ሁሉንም ተነሡ። "አይ፡ በጣም ጥሩ ነው፡" አልኩኝ። ሚስዮናውያኑ እጅግ ጥሩ ስራ ሰርተዋል፣ ስለዚህ እጅግ እናመሰግናለን።

4 አሁን፡ በሮሜ መጽሐፍ፡ 11ኛው ምዕራፍ 28ኛው ቁጥር። ቅዱስ ቃል ሲነበብ ከልባችሁ አዳምጡ።

> **በወንጌልስ በኩል፡ ስለ እናንተ ጠላቶች ናቸው፤ በምርጫ በኩል ግን፡** ስለ... **አባቶች ተወዳጆች ናቸው።**
>
> **እግዚአብሔር በጸጋው ሰጦታና** በመጥራቱ **አይጸጸትምና።**

5 እንጸልይ። ጌታ ሆይ ዛሬ ማታ በአክብሮት እና በቅንነት፡ በሙሉ ልባችን፡ ስንቀርብ፡ የተነገሩ ነገሮች ለክብርህ ብቻ ተነግረዋልና እርዳን። ጌታ ሆይ፡ እኔንንም እርዳኝ፡ማለት ያለብኝን እና ምን ያህል መናገር እንዳለብኝ በአእምሮዬ አኑርልኝ። ጊዜህ ሲሆን አቁመኝ። በጉባኤው ውስጥ ለታመሙ እና ለችግረኞች ጥቅም እያንዳንዱ ልብ እነዚህን ነገሮች እንዲቀበል እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጸለይኩ። አሜን።

6 አሁን፣ ጥቂቶች ብንሆንም በዚህ ርዕስ ጉዳይ መናገር እፈልጋለሁ። እናንተን—ለረጅም ጊዜ እንዳላቆያችሁ እጥራለሁ፡ ነገ ማታም ደግሞ

ደግማችሁ እንድትመጡ በጥሩ ሰአት እንድትወጡ የተቻለኝን እሞክራለሁ ሰዓቴን እዚህ አስቀምጫለው። አሁን በጸሎት ውስጥ ሁኑ። ልጁ ካርዶችን እንኳን የሚሰጥ አይመስለኝም። እኔም አልጠየቅኩትም… ቢሰጡም ወይም ቢሰጡም ባይሰጡም፡ ምንም አይደለም። ጥቂቶችን መጥራት ካስፈለገም ካርዶች እዚህ አሉ። እንዲህ፡ ካልሆነ ግን፡ እንዴት እንደሚሆን፡ መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገውን እናያለን።

7 አሁን፡ በደንብ አድምጡኝ… ምናልባት ይሄ ነገር፡ አሁን… ስለ እኔ… ስለ ግል ህይወቴ የሚያትት ነገር ነው—ጥቂቶች ስለሆንን፡ ይሄን ለመናገር ጥሩ ጊዜ ነው። እናም ዛሬ ማታ ይሄን ቃል ያነበብኩበት ምክንያት ለዚህ ነው፣ ስጦታዎች እና ጥሪዎች ማንም ሰው ሊያገኛቸው የማይቻሉ ነገር እንዳልሆኑ እንድታዩ ነው።

8 ጳውሎስ ሲናገር፡ እንዲህ አለ፡ “አይሁዶች፡ በወንጌል ምክንያት፡ ስለእኛ፡ ከእግዚአብሔር ርቀው ታውረዋል፡ ያም ስለ እኛ ነው።” ከዚያ በፊት ያለው ጥቅስ ግን፡- “እስራኤል ሁሉ ይድናል፡” አለ። እስራኤል ሁሉ ይድናል ይላል። በምርጫ በኩል፡ እንደ ቃሉ በአብራሃም ዘር በኩል ዓለምን ይባርክ ዘንድ አህዛብ የንስሓ ዕድል እንድናገኝ፡ እግዚአብሔር አባት፡ እየወደዳቸው፡ አይኖቻቸውን ዘጋው። የጌታ ሉዓላዊነት እንዴት እንደሆነ አያችሁ? ቃሉ ብቻ መፈጸም አለበት። ሌላው ሁሉ አይጠቅምም። እና አሁን እኛ፡ በ… እኛን መርጦናል፡ እግዚአብሄር አይሁድን መረጠ፡ እርሱም…

9 ስለ እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔር አስቀድሞ ያውቃል። እንዲህ ይሆናል ሲል፡ አስቀድሞ ስለሚያውቅ ነው። አሁን አምላክ፡ አምላክ ለመሆን፡ የመጨረሻው ከመጀመሪያ ማወቅ ይኖርበታል፡ ካልሆነ ግን ፍጻሜ የሌለው አምላክ ሊባል አይችልም። ማንም እንዲጠፋ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። በእርግጠኛነት አይደለም! ማንም እንዲጠፋ አይፈልግም። ነገር ግን በዓለም ቀኖች መጀመሪያ—ከጅምሩ ጀምሮ፡ እግዚአብሔር ማን እንደሚድን እና ማን እንደማይድን በትክክል ያውቃል። ህዝቡ እንዲጠፋ አይፈልግም “ሁሉንም ይድኑ ዘንድ ነው እንጂ፡ ማንም እንዲጠፋ ፈቃዱ አይደለም፡” ነገር ግን ከመጀመርያ ጀምሮ ማን ይድናል ማን አይድንም ያውቀዋል። በዚህም ምክንያት፡ “**እንዲህ** ይሆናል። **እንዲያ** ይሆናል።” ወይም፡ “**ይሄኛው እንዲያ** ይሆናል። **ያኛው** ሰው **እንዲህ** ይሆናል ይላል።” አያችሁ?

10 ፍጻሜ የሌለው ስለሆነ አስቀድሞ ያውቀዋል። ይህ ማለት፡ ምን እንደሆነ ከገባችሁ፡- “የማያውቀው ነገር የለም።” አያችሁ፡ ያውቃል። አያችሁ፡ ከጊዜ በፊት ይሁን፡ ጊዜ ከመጥፋቱ በኋላ፡ እርሱ፡ የማያውቀው ነገር የለም። ሁሉም ነገር በአእምሮው ውስጥ ነው። ጳውሎስ በሮሜ፡ ምዕራፍ 8 እና 9 ላይ ሲናገር፡ “እንግዲህ ስለ ምን እስከ አሁን ድረስ ይነቅፋል? ” ሲል እናያለን፡ ጌታ ግን…

11 ወንጌልን እንደ መሰበክ። አንድ ሰው “ወንድም ብራንሃም፣ ይህን ታምናለህ? ” አለኝ፡

“ይሄውልህ፡” አልኩት።

“ካልቪኒስት ሳትሆን አትቀርም፡” አለኝ።

“ካልቪኒስት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እስካለ ድረስ ካልቪኒስት ነኝ፡” አልኩት።

12 አሁን፡ በአንድ ዛፍ ላይ ቅርንጫፍ ይኖራል፡ ይህም ካልቪኒዝም ይባላል፡ ነገር ግን በዛፉ ላይ፡ ሌሎች ቅርንጫፎችም አሉ። አንድ ዛፍ ከአንድ በላይ ቅርንጫፎች አሉትና። በዚያው ወደ ዘላለማዊ ደህንነት ማስኬድ ይፈልጋል፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ወደ ዩኒቨርሳሊስም ተመልሳችሁ አንዱ ቦታ ላይ ትወድቃላችሁ፡ መጨረሻ የለውም። ነገር ግን ካልቪኒዝምን ስትደርሱበት፡ አርመንያኒዝም ትጀምራላችሁ። እነሆ፡ በዛፉ ላይ ሌላ ቅርንጫፍ፡ ዛፉ ላይ ሌሎች ቅርንጫፎችም ይወጣሉ፣ ይቀጥላል። እነዚህ ሁሉ ተደምረው ዛፍ ይሰራሉ። ስለዚህ ከቅዱሳት መጻሕፍት እስካልወጣ ድረስ በ—በካልቪኒዝም... አምናለሁ።

13 እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን በክርስቶስ እንደ መረጣት፡ እና ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ ክርስቶስን ስለሷ መስዋዕት እንደሚያደርገው እና እንደሚያውቅ አምናለሁ። “ዓለም ከመፈጠሩ በፊት የታረደው የእግዚአብሔር በግ፡” ይለዋል ቅዱስ ቃል። አያችሁ? ኢየሱስም ዓለም ሳይፈጠር በፊት አውቃችኋለሁ ብሎናል፡ ጳውሎስ እንዲህ አለ፦ “እሱ—አስቀድሞ አውቆን በኢየሱስ ክርስቶስም ልጆች እንድንሆን ዓለም ሳይፈጠር በፊት አስቀድሞ ወስኖናል።” ይሄ ነው እግዚአብሔር። ይህ ነው አባታችን። አያችሁ?

14 ስለዚህ አትጨነቁ፡ መንኮራኩሮቹ በትክክል እየዞሩ ናቸው፡ ሁሉም ነገር በጊዜው እየመጣ ነው። ብቸኛው ነገር፡ ዙረቱ ውስጥ፡ ግቡ። ነገርየው—ደስ የሚለው ክፍሉ ይህ ነው፡ ውደ ዙሩ ስትገቡ እንዴት መስራት እንደሚገባችሁ ታውቃላችሁ።

15 አሁን፡ ይሄን አስተውሉ፦ “ስጦታዎች እና ጥሪዎች ንስሓ አይጠይቁም፡” በጌታ ዘንድ የተሰጠኝ ጥሪ—በቅዱሳት መጻህፍት ማሳየት የምችልበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው። ስለዚህ ዛሬ ማታ የግሌን ነገር አድርጋችሁ በማታስቡ ነገር ግን ጌታ ያደረገው ዘንድ ያለውን ነገሮች፡ አውቃችሁ እና ተገንዝባችሁ—ደስ የሚል ነገር እንድታዩበት እና እንድትከተሉት፡ በምትችሉ ወዳጆቼ ዘንድ መኖሬ አምኛለሁ።

16 አሁን ከሁሉ በፊት፡ የማስታውሰው የመጀመሪያው ነገር፡ ራዕይ ነው። በአእምሮዬ የማስታውሰው የመጀመሪያው ነገር ጌታ የሰጠኝ ራእይ ነው። ይህም ከብዙ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት፡ ገና ጨቅላ ልጅ በነበርኩ ጊዜ ነው። በእጄም ድንጋይ ይዤ ነበር።

17 አሁን፡ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡ ረጅም ቀሚስ ለብሼ አስታውሳለሁ። ትናንሽ ወንዶች ልጆች ረዥም ቀሚስ ሲለብሱ ምናልባት (ከእናንተ መካከል) የምታስታውሱ ሰዎች ካላችሁ አላውቅም። ልጆች ረዥም ቀሚስ ሲለብሱ የምታስታውሱ፡ ስንቶች፡ አላችሁ? ደህና፡ እኔ በምንኖርባት ትንሽዬ ጎጆአችን ውስጥ፡ ወለሉ ላይ እየተሳበኩ፡ አስታውሳለሁ። እና አንድ ሰው ነበር፡ ማን እንደሆነ አላውቅም፡ እና ገባ። እና እማማ—በቀሚሴ ላይ ትንሽ ሰማያዊ ሪባን ሠርታልኝ ነበር። እና ገና መራመድ አልቻልኩም ነበር። ያን ጊዜ ዳዴ እል ነበር፣ እና ጣቴን በእግሩ ላይ ባለው በበረዶው ውስጥ አጣብቄ፣ ከማገዶው በሚወጣው ሙቀት ለመሞቅ ከቆመው ሰው እግር ላይ በረዶ ሰበላ ነበር። እናቴም መጥታ ስታነሣኝ አስታውሳለሁ።

18 ከዚያ በሁለተኛ ደረጃ የማስታውሰው ነገር፡ ከሁለት ዓመታት በኋላ ይመስለኛል፡ እጄ ላይ ድንጋይ ይዤ ነበር። እና ያኔ የሦስት ዓመት ልጅ ሆኛለሁ፣ ታናሽ ወንድሜም የዚያን ጊዜ ገና ሁለት ዓመት ያልሞላው ነበር። እናም የእንጨት የቆየ ቦታ ላይ ከጓሮው ጀርባ ላይ ነበርን። ቦታውም እንጨት አምጥተው የሚቆራርጡበት ስፍራ ነው። በጓሮው ውስጥ እንጨቱን አምጥተው የሚቆራርጡበት ዘመን ስንቶቻችሁ ታስታውሳላችሁ? ዛሬ ማታ እንኳን ክራባት ሊብሻለሁ? አ—ቤት ውስጥ ነኝና።

19 ከዚያም ያኔ... በዚያ አሮጌው ጓሮ ውስጥ፡ ከወንዝ ምንጭ የተረፈች አነስተኛ ቅርንጫፍ በዚያ ነበረች። ሌላም በምንጩ ላይ አጥልቀን ውሃን የምንቀዳባት ቀድተንም ያረጀ ባልዲ፡ ያረጀ የጥድ ባልዲ ውስጥ፡ ቀድተን የምናመጣባት ቅል ነበረች።

20 ምስኪን አሮጊቷ አያቴ ከመሞቷ በፊት ባየኋት ጊዜ ትዝ ይለኛል፡ የመቶ አስር አመት አሮጊት ነበረች። ስትሞትም፡ ከመሞቷ በፊት እጆቼ ላይ እንዲህ ወደ ላይ ከፍ አድርጌ አነሳኋት። እሷም እየሞተች፡ እጆቿን እኔ ላይ አድርጋ፦ “የኔ ማር፡ አሁን እና እስከ ዘለአለም ድረስ፡ ጌታ ነፍስህን ይባርካት፡” አለችኝ።

21 ሴትየዋ፡ በዘመኗ ሁሉ—አንዲት የርሷ ጫማ የነበረቻት አይመስለኝም። ወጣት በሆንኩ ጊዜም፡ ልጠይቃቸው በሄድኩ ቁጥር፡ ሳያት አስታውሳለሁኝ፡ ዘወትር ማለዳ ተነስታ፡ እስከ ምንጩ ድረስ፡ በባዶ እግሯ በረዶ ላይ ትሄድና፡ እግሮቿ እንደዚያ እንደሆኑ፡ አንድ ባልዲ ውሃ ቀድታ ትመጣለች። ስለዚህ ቅር አይበላችሁ፡ አንድ መቶ አስር ዓመታት ኖራለች። ደግሞም (አዎን፡ ጌታዬ) በጣም፡ በጣም ጨካኝ ነበረች።

22 ስለዚህ አባቴ በልጅነቱ ስለተጫወተባቸው ብዬዎች ልትነግረኝ እንደነበረ አስታውሳለሁ። “እና እቺ ምስኪን አሮጊት፣” እንዲህ አልኩ፡ “ወደ ቆጡ እንዴት ብላ ትወጣዋለች አልኩ? ” አነስተኛ፡ ባለ ሁለት-ክፍል ከእንጨት የተሰራች ጎጆ፡ ከጣራዋ በታች ውስጥ ቆጥ ነበረች። መወጣጫ እንዲሆን፡ ከሁለት ችግኞች ተቆርጦ የተዘጋጀላት መሰላል፡ ነበረባት። እናያለን፡ አልኩኝ...

23 አሁን፡ ከእራት በኋላ፡ አለችኝ፦ “የአባትህ—ብዬዎችን፡ አሳይሃለሁ፡ እነግርሃለሁ፡” ብላኛለች።

እኔም “እሺ፡” አልኳት።

24 እንደ ጥንት ሰዎች ንብረቷ ካስቀመጠችበት ቆጥ ላይ ካለው ቀፎ ውስጥ ልታሳየኝ ፈልጋለች። እኔም አሳብ ገብቶብኛል፦ “ይህች ምስኪን አሮጊት ይሄን መሰላል እንዴት ልትወጣው ነው? ” ወደ እሷ ዞርኩና፦ “አያቴ፡” አልኳት፡ “አሁን፡ ቆይ የኔ‘ናት፡ እኔ ቀድሜሽ ልውጣና ልርዳሽ፡” አልኳት።

25 “ዞር በል፡” ብላኝ፡ መሰላሉን እንደ ሽኮኮ ወጣች። በል “አሁን ና!” አለችኝ።

“እሺ፡ አያቴ፡” አልኳት።

26 እና አሰብኩት፦ “ኦህ፡ ማይ፡ በአንድ መቶ አስር አመቴ፡ እንዲህ ያለ ብርታት በኖረኝ!”

27 ሌላው፡ ትዝ የሚለኝ በውሃው ምንጭ አጠገብ ሆኜ፡ ድንጋይ በእጄ ይዤ ምን ያህል ብርቱ እንደ ሆንኩ ወንድሜን ለማሳየት፡ ድንጋዮቹን ጭቃው

ላይ፡ እንዲህ እየወረወርኩ እስታውሳለሁ። እና ዛፍ ላይ አርፎ ወዲያ ወዲህ እያለ፡ የሚዘምር፡ ምስኪኑ ሮቢን ወይም ሌላ ዓይነት ወፍ ነበር። እና፡ ይህ ምስኪን ሮቢን፡ የተናገረኝ መሰለኝ። የተናገረኝን ለመስማት ዞር ስል፡ ወፏ በረረ፡ ድምጽም፦ "የህይወትህ አብዛኛው ክፍል ኒው አልባኒ ከምትባል ከተማ አቅራቢያ ትኖራለህ" አለኝ።

28 ካደኩበት ቦታ የሶስት ማይልስ ርቀት ርቃ የምትገኝ ከተማ ናት። ከአንድ አመት በኋላ፡ እንሄዳለን የሚል፡ ምንም አይነት ሐሳብ ሳይኖረን፡ ወደ ኒው አልባኒ... ሄድን። በህይወት ውስጥ ባለፍኩባቸው፡ እነዚያ ነገሮች...

29 ይታያችሁ፡ ቤተሰቦቼ፡ የሐይማኖት ሰዎች አልነበሩም። አባቴ እና እናቴ ቤተክርስትያን አይሄዱም። ከዚያ በፊት ግን፡ ካቶሊኮች ናቸው።

30 ካልተሳሳትኩ፡ የወንድሜ ልጅ፡ ዛሬ ማታ እዚህ ጉባኤ ውስጥ ያለ ይመስለኛል። ወታደር ነው። እሱ እራሱ ካቶሊክ ነው፡ እስከ አሁን ድረስ ካቶሊክ ነው። ሰለሱ እየጸለይኩ ነው። ትላንት ማታ ግን፡ እዚህ በመድረኩ በነበረ ጊዜ፡ እነዚያን የእግዚአብሔር ነገሮችን አይቷል። ለብዙ ጊዜ በግዳጅ ርቆ የነበረ ሰው ነው፡ እና እንዲህ አለ፡ ቆሞ፡ እንዲህ አለኝ፦ "አጎቴ ቢል?" አለኝ፡ "እነዚህ ነገሮችን ሳይ... " "እነዚህ ነገሮች—በካቶሊክ ቤተክርስትያን ውስጥ የሉም፡" አለኝ። እንዲህ አለ፡ "እና... አጎቴ ቢል፡ አንተ—ትክክል እንደሆንክ አምኛለሁ፡" አለኝ።

31 እኔም እንዲህ አልኩት፦ "ሃኒ፡ ትክክለኛው **እኔ** አይደለሁም፡ ትክክለኛው እርሱ ነው። አየህ፡ ትክክለኛው **እርሱ** ነው።" እሱ እንዲህ... እኔም እንዲህ አልኩት፦ "ሜልቪን፡ አሁን እኔ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሙሉ ልብህ፡ እንድታመልከው እንጂ እንዲህ አድርግ የምልህ ነገር የለኝም። መሄድ ወደፈለግከው ሂድ። ነገር ግን አስተውል፡ በልብህ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በልብህ እንደ አዲስ እንደተወለደ እርግጠኛ ሁን። ከዚያ በኋላ ወደፈልግከው ቤተክርስትያን መሄድ ትችላለህ አልኩት።"

32 አሁን ግን፡ ከእኔ በፊት የነበሩ ሰዎች ካቶሊኮች ናቸው። አባቴ አይርሻዊ ነው እናቴም አይርሽ ናት። ከአይርሽ ደም የተቀላቀለብን ብቸኛው ነገር አያቴ ቸርኬ ህንዳዊት መሆኗ ብቻ ነው። እናቴ በግማሽ-ዲቃላ ናት። እና ስለዚህ እኔ... ለእኔ፡ የእኔ... የእኛ ትውልድ፣ ከሦስት በኋላ፣ ጠፍቷል። ነገር ግን ጥብቅ አይሪሽ ከመሆን የሚገድብ ብቸኛው ነገር ይህ ነበር፡ ሃርቪ እና ብራንሃም ነን። እስከ አሁን ድረስ አይሪሽ የሆነው፡ ሊዮን የሚባል አለ። እና ሁሉንም ካቶሊኮች ነበሩ። እኔ ግን፡ ልጆች ሆነን፡ ሃይማኖታዊ ልምምድ ይሁን ትምህርት አልነበረንም።

33 እነዚህ ስጦታዎች፡ ራዕዮች ግን፡ አሁን እንደማያቸው አድርጌ ያኔም አያቸው ነበር፡ እውነት ነው፡ ምክንያቱ ስጦታዎች እና ጥሪዎች ያለንስሓ የሚሰጡ ናቸው። የእግዚአብሄር የቀደመ እውቀቱ ነው የሚሰራው ጌታ ነው። እኔ ግን በህይወቴ ሁሉ ስለዚህ ጉዳይ ለመናገር እፈራ ነበር።

34 **ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፣ ዛሬ እና ለዘላለም ያው ነው፡** በተባለው ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ ታሪኬን አንብባችሁታል። በአንዳንድ መጻሕፍት ውስጥ፡ ያለ ይመስለኛል። ትክክል ነኝ፡ ጂን? በዚህኛው በመደበኛው—በመደበኛው መጽሐፍ ውስጥ፡ አሁን ባለን—መጽሐፍ ውስጥ ነው? **የህይወት ታሪክ**፡ ነው? ነው መሰለኝ። እና ያሉንን... አይገርምም ግን? መጻሕፍቶቹ ሆነው፡ እኔ

እራሴ፡ ፈጽሜ አንብቤአቸው አላውቅም። የጻፋቸው ሌላ ሰው ነው፡ ከየጉባኤው ያገኟቸው ነገሮች ናቸው። በዚህ ሁሉ ቆይቻለሁና፡ አሁን ግን አንዳች ልዩ ነገር እንዲሆን እጠብቃለሁ። ብቻ፡ ይሁን፡ ደህናም ናቸውና፡ አሁን ግን ጊዜ ባገኘሁ ቁጥር፡ ከዚህም ከዚያም የተወሰነውን ክፍል አነብቤአቸዋለሁ።

35 አሁን ይህ ሁሉ፡ በእንዲህ እንዳለ፡ ገና የሰባት ዓመት—ህጻን ልጅ ሳለሁ፡ በራእይ የተናገረኝን፡ ታውቃላችሁ፡ ሲናገረኝም፦ "አንተ ስታድግ የምትሰራው ስራ ስላለ ሰውነትህን ከሚያረክስ ሁሉ ራቅ፡ እንዳትጠጣ ወይም እንዳታጨስ" አለኝ። እናንተም ይሄን ከመጽሐፍ ሰምታችኋል። አዎን፡ ትክክል ነው። ይህ ግን በተደጋጋሚ መፈጸሙን ቀጠለ።

36 አገልጋይ ከሆንኩ በኋላ፡ አዎን፡ ከዚያ በኋላ'ማ—ከዚያ በኋላ ሁሌጊዜ መሆን ጀመረ።

37 አንድ ቀን ማታ ግን ጌታችን ኢየሱስን አየሁት። ይሄን እንድናገር፡ ከመንፈስ ቅዱስ፡ ፈቃድ እንዳገኘሁ አምናለሁ። ያንን የሚመጣ የእግዚአብሔር መልአክ ጌታ ኢየሱስ አይደለም። በዚያ ራዕይ ውስጥ እርሱን አይመስለውም። ምክንያቱ፡ ጌታችን ኢየሱስን በራዕይ እኔ ሳየው፡ ሰውነቱ አነስ ያለ ሰው ነው። ግዙፍ አልነበረም... ስለ አባቴ እየጸለይኩ፡ ማሳው ላይ ጊዜ አሳልፌ ነበር። ተመልሼም ገባሁና ወደ አልጋየ ሄድኩ፡ በዚያም ምሽት ላይ እርሱን—አይቼ "አምላክ ሆይ፡ አድነው!" አልኩኝ፤

38 እናቴ ድናለች እናም አጥምቄአታለሁ። ከዚያም እንዲህ አሰብኩ፡ "ኦህ፡ አባቴ በጣም ይጠጣል።" "ጌታ ኢየሱስን እንዲቀበል ባደርግ ኖሮ!" ብየ አሰብኩ፤ ወጣሁና፣ ከፊተኛው ክፍል ውስጥ፣ በሩ አጠገብ ባለው ትንሽ ያረጀ የሳር ፍራሽ ላይ ተኛሁ።

39 እና የሆነ ነገር "ተነሳ፡" አለኝ። ተነሳሁኝና፡ ከኋላየ ከጓሮ ወዳለው፡ የደረቀ ሰርዶ እና ሳር፡ ወዳለበት ማሳ ወጣሁ።

40 በዚያም፡ ከእኔ ከአሥር ጫማ የማይበልጥ ርቀት ላይ፡ አንድ ሰው ቆሟል፤ ነጭ ልብስ የለበሰ ሰውነቱም አነስ ያለ፤ አጠር ያለ፤ ጢማም፡ ያራሰ ጸጉሩ ትከሻው ድረስ የወረደ፤ እጆቹንም **እንዲህ** አጣጥፎ፤ እጅግ-ሰላማዊ መልክ ያለው፡ እንደዚህ ሆኖ፤ ከእኔ ወደ ጎን ይመለከት ነበር። ሊገባኝ ያልቻለ ነገር ግን፣ እግሮቹ እንዴት፡ አንደኛው ከሌላኛው ጀርባ መሆኑ ነው። ንፋሱም እየነፈሰ፡ ልብሱ ይንቀሳቀሳል፡ ሰርዶውም ይወዛወዛል።

41 "እንዴ፤ ቆይ እስኪ፡" ብየ አሰብኩ። እራሴን በእጄ መታ መታ አረግኩ። "እንዴ፡ እኔ አልተኛሁም፡" አልኩኝ። ጎንበስ አልኩና፡ ከሰርዶው ትንሽ ቀንጠስ አድርጌ፡ ልክ እንደ፡ የጥርስ እስቴኪኒ ወሰድኩ። በአፌም ውስጥ አረግኩት። ወደ ቤት ዞር ብየ አየሁ። "አይ፤ ቤት ውስጥ ለአባቴ እየጸለይኩ ነበር፣ የሆነ ነገር ግን ወደዚህ ውጣ አለኝ፣ እና በዚህም ይህ ሰውዬ ቆሟል፡" አልኩኝ።

42 "ጌታ ኢየሱስን ይመስላል፡" ብየ አሰብኩ። "እርሱ ሳይሆን አይቀርም? " ብየ አሰብኩ፡ በትክክል ቤታችን ወዳለበት አቅጣጫ፡ እየተመለከተ ነበር። ምናልባት ላየው ከቻልኩ ብየ **በዚህ** በኩል አቅጣጫየን ቀየርኩ። ፊቱን በጎን በኩል እንዲህ ታየኝ። እሱ ግን... እሱን ለማየት **በዚህ** በኩል ሙሉ ለሙሉ መዞር ነበረብኝ። እና "እሕሕም!" አልኩኝ፡ አልተንቀሳቀሰም። እና "ልጠራው

እኮ እችላለሁ፡” ብየ አሰብኩ። እና “ኢየሱስ፡” አልኩኝ። እና እሱም ሲዞር፡ **እንዲህ** ዙርያውን ቃኘ። እጆቹንም ዘረጋ፡ እኔ የማስታውሰው ይህ ብቻ ነው።

43 የእሱን ምስል የፊቱን ገጸ ባህሪያት፡ ለመሳል የሚችል ሰዓሊ በአለም ላይ የለም። እስካሁን ካየኋቸው የተሻለ **የሠላሳ-ሶስቱ የሆፍማን የክርስቶስ ራስ ነው፡** በጽሑፎቼ እና በምጠቀማቸው ነገሮች ሁሉ ላይ ይገኛል። ያ ልክ እንደዚያ ስለሚመስል ነው፡ ወይም ደግሞ... በጣም ቅርብ፣ በተቻለ መጠን ይቀርበዋል።

44 በምስሉም፡ ሰው ይመስላል፣ እሱ ቢናገር ግን፣ ዓለም ትጠፋለች፣ ይሁን እንጂ የሆነ ነገር—እስክትሆኑ ድረስ እጅግ የበዛ ፍቅር እና በጎነት ነበረው... እኔ ራሴ ተወረወርኩ። ከዚያ በኋላ፡ ወደ ራሴ ስመለስ፡ ሊነጋጋ ሲል እራሴን በቀን ብርሃን ላይ፡ ከሰርዶው ማሳ፡ ወደ ቤት ስመለስ፡ የፒጃማ ሸሚዜ፡ በእንባ ርሶ አገኘሁት።

45 አገልጋይ ለነበረ ጓደኛየ አጫወትኩት። እሱም “ቢሊ፡ ይሄ ነገር ያሳብድሃል፡” አለኝ። እንዲህ አለኝ፡ “ዲያብሎስ ነው።” “በእንዲህ አይነት ነገሮች እራስህን አታታልል፡” አለኝ። በዚያ ጊዜ የባፕቲስት አገልጋይ ነበርኩ።

46 ከዚያ በኋላ፡ ወደ ሌላ ጓደኛዬ ሄድኩኝ። ቁጭ አድርጌ ስለ ጉዳዩ ነገርኩት። “ወንድሜ፡ ስለዚህ ጉዳይ ምን ታስባለህ? ” አልኩት፤

47 “ችግር የለውም፡ ቢሊ፡ እኔ እነግርሃለሁ፡” አለኝ። እሱም አለኝ፦ “ህይወትህን መጠበቅ ከፈለግክ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን፡ ስለ እግዚአብሄር ጸጋ ወዘተ ብቻ መሰበክ እንዳለብህ አምናለሁ፡ እንደነዚህ በመሳሰሉ፡ እንግዳ ነገሮች መወሰድ አልፈልግም።”

48 እኔም “ጌታዬ፡ እንግዳ የሆኑ ነገሮችን መከተል አልፈልጉም፡” አልኩት። “እኔ የፈለግኩት ይህ ነገር ምን እንደሆነ ማወቅ ብቻ ነው፡” አልኩት።

49 እሱም፦ “ቢሊ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት እነዚህ ነገሮች በቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ነበሩ። ነገር ግን፡” አለኝ፡ “ሐዋርያት ሁሉ ከሞቱ በኋላ፡ እነዚህ ነገሮችም አብረው ሞቷል።” እንዲህም አለኝ፦ “አሁን ግን እነዚህን ያሏቸው... የሚያዩ ብቸኛ ነገሮች፡” “መናፍስታውያን፡ አጋንንት፡” ይባላሉ አለኝ።

“ኦህ ወንድም ማኪኒ፡ እውነትህን ነው? ” አልኩት፤

“አዎን፡ ጌታየ፡” አለኝ።

እኔም ወድያው፦ “አምላክ ሆይ፡ ይቅር በለኝ!”

50 እንዲህ አልኩት፦ “ኦህ፡ ወንድም ማኪኒ... እ—እ፡ እባክህ—በጸሎት አብረኸኝ ትሆናለህ ጌታ ፈጽሞ እንዲያርቅልኝ አብረኸኝ ጸልይ? እኔ እሱን እንደምወደው እና በዚህ ነገር እርሱን ማሳዘን እንደማልወድ ታውቃለህ።” “አብረን እንጸልይ፡” አልኩት።

51 “እሺ እጸልያለሁ፡ ወንድም ቢሊ፡” አለኝ። ወድያውም ለአገልጋዮች—በተለየው ክፍል አብረን ጸለይን።

52 ብዙ አገልጋዮችን ጠይቄአለሁ። መልሳቸውም ተመሳሳይ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ዲያብሎስ አርገው እንዳያስቡኝ፡ እነሱን መጠየቅ ፈራሁ። ስለዚህ—እንደዚያ መምሰል አልፈለግኩም። በልቤ ውስጥ የተፈጸመው ነገር እኔ

አውቀዋለሁ። ይሄው፡ ይህ ነው፡ በልቤ ውስጥ—የተፈጸመ አንዳች ነገር ነበር። እንደዚያ እንዲያስቡኝ ግን ፈጽሜ አልፈልገውም፡ በፍጹም።

53 ከብዙ ዓመታት በኋላ፡ በወቅቱ እኔ አባል የነበርኩባት የመጀመርያዋ የባፕቲስት ቤተክርስትያን ውስጥ አንድ ነገር ሰማሁ፡ አንድ ሰው “ትናንት ማታ፡ ሄዳችሁ ወንበር-ሰባሪዎቹን ልትሰሟቸው ይገባ ነበር፡” ሲል ሰማሁ።

54 “ወንበር ሰባሪዎች? ” አልኩኝ፤ ዋልት ጆንሰን፡ የተባለው የባስ ዘማሪ የሆነው ጓደኛየን፡ እንዲህ አልኩት፡- “ምን ማለት ነው፡ ወንድም ዋልት? ”

“እነዚህ ጴንጤቆስጤዎች ናቸዋ፡” አለኝ።

“ምን? ” አልኩት፤

55 “ጴንጤቆስጤዎች!” ናቸው አለ፤ “ቢሊ፡ እነሱን ብታያቸው ኖሮ፡” አለኝ፤ “መሬት ላይ እንዲህ ይንከባለላሉ ወደ-ላይ-ወደታች ይዘላሉ፡” አለኝ። “በማይታውቅ ልሳን ካልተናገሩ በቀር—አንድንም ብለው ያሰባሉ፡” በማለት ነገረኝ።

“የት ይገኛሉ? ” ብየ ጠየቅኩት፤

56 “ኦህ፡” “በሎይስቪል ማዶ፡ አነስተኛ የዳስ ጉባኤ አርገዋል፡” አለኝ። “በርግጥ፡ ጥቁሮች ናቸው፡” አለ።

“እህ-ህ፡” አልኩ።

አክሎም “አረ ብዙ ነጮችም አሉበት፡” አለ።

“እነርሱም፡ እንደዚሁ ያደርጋሉ? ” ብየ ጠየቅኩት፤

“አዎን፡ አዎን! እነርሱም፡ ያው ናቸው፡” አለኝ።

57 “ሰዎቹ በእንደዚህ አይነት ነገሮች ይደባለቃሉ´ዴ አስቂኝ ነው፡” አልኩት። “ይገርማል፡ እኛም እንዲህ ሊኖረን ይገባል፡” አልኩኝ። እሁድ ጠዋት ነበረች፡ ፈጽሜ አልረሳትም። በምግብ አለመፈጨት ችግር የደረቀ የብርቱካን ልጣጭ እየበላ ነበር፡ እና ልክ እንደ ትላንትና ሆኖ ትዝ ይለኛል። አሰብኩበት፡- “ልሳን መናገር፡ ወደላይ-ወደታች መዝለል፡ ቀጥለውስ ምን አይነት ሃይማኖት ሊያሰሙን ይሆን? ” ብየ ሄድኩኝ—ቀጠልኩኝ።

58 ከዚያ በኋላ አንድ ሽማግሌ፡ ምናልባት ዛሬ በዚህ ቤተክርስትያን ይኑር አይኑር እንጃ፡ እዚህ ቤተ ክርስትያን ያለው፡ ጆን ሪያን የተባለ ሰው ተዋወቅኩኝ። አንድ ቦታ ላይ ተዋወቅኩት... ሽማግሌው ረዥም ጺም እና ጸጉር ያለው ነው፡ ምናልባት እዚህ ሊኖር ይችላል። እዚህ ጋር ሃውስ ኦፍ ዴቪድ ከሚገኘው ቤንተን ሃርበር፡ አድርጌ አሰቤው ነበር።

59 እና በሎይስቪል ውስጥ ቦታ ነበራቸው። ሰዎችን ለማግኘት ሞከርኩኝ፡ ነቢያት ጉባኤ ብለው ይጠሯቸዋል። ስለዚህ ሄጄ ምን እንደሆነ ለማየት አሰብኩ። ደረስኩኝ፡ ማንም ሰው መሬት ላይ ሲንከባለል አላየሁም፡ አንዳንድ እንግዳ ትምህርቶች ግን ነበሯቸው። ወደ ቤቱ እንድመጣ ጋብዞኝ የነበረውን ሽማግሌ፡ የተዋወቅኩት በዚያ ነበር።

60 እና ለመዝናናት ሄድኩኝ። አንድ ቀን ወደዚያ ሄድኩና፡ ወደ ቤቱም ልድረስ ብየ ሄድኩ፡ እሱን ግን አላገኘሁትም፡ ኢንዲያናፖሊስ ወደሚገኝ አንድ ቦታ ሄዶ አገኘሁት። ሚስቱ፡ “ጌታ ጠርቶት ሄዷል፡” አለችኝ።

“አንቺ ግን እንዲሁ ሲሄድ ዝም አልሽው ማለት ነው? ” አልኳት፤

61 “እንዴ፡ የእግዚአብሄር ባርያ'ኮ ነው!” አለችኝ፤ ምስኪን አሮጊት፡ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት መሞቷን ሰምቻለሁ። ለባልዋ ሚች ነበረች። ማይ፡ ሚስት ማለት እንዲህ ናት! አዎን። ይሳሳት አይሳሳት፡ ሁሌ ትክክል ነው! እኔም... አዎን፡ አውቃቸዋለሁ አልኳት...

62 እና እሱ... ወንድም ሪያን የት ነህ፡ እዚህ አለህ? የለም መሰለኝ። ትላንት፡ እዚህ ነበር አይደል፡ ወጣቶች?

63 እንደው፡ በቤታቸው የሚላስ የሚቀመስ አልነበራቸውም፡ እና ባገኙት ነገር የሚኖሩ ሰዎች ናቸው። እውነት ነው። እና ሚቺጋን ካለው ኩሬ፡ ማለቴ ሐይቅ፡ አሳ አጥምጄ፡ እየተመለስኩ ነበርና—ወደዚያ ቤት መጣሁ። ሌላው ይቅር፡ አሳውን የሚጠብሱበት ጮማም ይሁን ቅባት፡ እንኳን አልነበራቸውም። እኔም “ቤት ውስጥ ያለ ምንም ነገር ትቶሽ ሄደ? ” አልኳት፤

“ኦህ፡ ወንድም ቢል፡ እሱ'ኮ የእግዚአብሄር ባርያ ነው!” አለችኝ፤ “እሱ... ” አለች፤

64 እኔም “መልካም፡ ልብህን እግዚአብሄር ይባርክ። ወንድሜ፡ እኔ ከጎንህ እቆምልሃለሁ፡” ብየ አሰብኩኝ። እውነቴን ነው። “ስለ ባሎቻችሁ ይሄን ያህል ለምታስቡ፡ በዚህ ምክንያት ከጎናችሁ ለመቆም ሁሌም ዝግጁ ነኝ።” የእውነቴን ነው። ዛሬ ዛሬ እንዲህ ያሉ ሴቶች፡ እና ሚስቶቻቸውን በዚህ መልኩ የሚያስቡ ብዙ ወንዶች ያስፈልጉናል። እውነት ነው። ባሎች እና ሚስቶች እንዲህ እጅ ለእጅ ቢያያዙ ኖሮ አሜሪካ የተሻለች ትሆን ነበር። ቢሳሳት ባይሳሳት፡ ከጎናቸው ሁኑ። እንዲህ ቢሆን ፍቺ አይበዛም ነበር።

65 ከዚያ በኋላ—ሄድን... ከዚያ ሄድኩኝ። ወደ ቤት እየተመለስኩ ሳለሁ፡ በሚገርም አጋጣሚ፡ በሚሽዋካ በኩል ማለፍ ነበረብኝ። እና አነስ—አነስ ያሉና ያረጁ መኪኖች፡ መንገድ ዳር ቆመው፡ አየሁ... “ኢየሱስ ብቻ፡” የሚል ጽሑፍ ተጽፎባቸዋል። “ምን ማለት ነው... 'ኢየሱስ ብቻ፡' መንፈሳዊ መሆን አለበት፡” አልኩኝ። ከዚያ ጠጋ አልኩና አየሁ ብዙ ብስክሌቶች “ኢየሱስ ብቻ፡” ተጽፎባቸዋል። ካዲላኮች፣ ሞዴል-ቲ የሆኑ ፎርዶች፣ ወዘተረፈ፣ “ኢየሱስ ብቻ” የሚል ጽሑፍ ተጽፎባቸዋል። “ይገርማል፡ ምን ይሆን? ” ብየ አሰብኩ፤

66 ተከታትየ ደረስኩና፡ መንፈሳዊ ጉባኤ እንደነበረ፡ አስተዋልኩ፡ ከሺ አምስት መቶ እስከ ሁለት ሺ የሚደርስ ህዝብ ተሰብስቦ ነበር። እዚያ ሲጮሁ እና ወደላይ-ወደ-ታች፡ እየዘለሉ ሲሄዱ ሰማሁ። “በል በል፡ ዛሬ ወንበር-ሰባሪዎቹን እዚህ አያቸዋለሁ፡” ብየ አሰብኩ።

67 አሮጌው ፎርድ ነበረኝ፡ ታውቋታላችሁ፡ በሰአት ሰላሳ ማይል ትበራለች የምላችሁ፡ አሥራ አምስት **ወደዚህ** እና አሥራ አምስት ወደ ላይ እና ወደ ታች **ወደዚያ** የምትበር። መኪና ማቆሚያ፡ እንዳገኘሁ... መንገድ ዳር ላይ አቁሜ፡ ወደ ጎዳናው ተመልሼ ሄድኩ። ገባሁ፡ ዙርያውን ቃኘሁ፡ መቆም የሚችል ሁሉ ቆሟል። ከራሶቻቸው በላይ ማየቴ ግድ ሆነብኝ። ይጮኻሉ፣ ይዘላሉ፣ ይወድቃሉ፣ ይንቀጠቀጣሉ። “ኧረ፡ እንዴት ያለ፡ ህዝብ ገጠመኝ!” ብየ አሰብኩ፤

68 በቆየሁ ቁጥር ግን የተሻለ ስሜት ተሰማኝ። “በጣም ደስ ይላል፡” አልኩኝ። “እነዚህ ሰዎች ችግር የለባቸውም፤ ዕብዶችም አይደሉም።” አልኩኝ። ከመካከላቸው አንዳንዶቹን አነጋግሬ፡ መልካም ሰዎች—ናቸው። ስለዚህ አልኩኝ...

69 ስለዚህ፡ አሁን፡ ምሽቱን ሁሉ በዚያ ጉባኤ አሳለፍኩና ሌሊቱን በዚያ አደርኩ፡ በሚቀጥለው ቀን እንደገና ገባሁ። በህይወት ታሪኬ ላይ ይሄን ስናገር ሰምታችኋል። በዚያም መድረክ አንድ መቶ ሐምሳ፡ ወይም ሁለት መቶ እና ከዚያ በላይ፡ በሚያክሉ አገልጋዮች መካከል ቆሜአለሁ፣ እየተነሳን ከየት እንደመጣን እንድንናገር ተጠየቅን። እኔም ወጣሁና፡- “ወንጌላዊ ዊልያም ብራንሃም፡ ባፕቲስት፡” ብየ ቁጭ አልኩ፡ “ከጀፈርሰንቪል፡” አልኩና፡ ቁጭ አልኩ። ሁሉም ከየት እንደመጡ ተናገሩ።

70 በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ስገባ... ማታ ሱሪዎቼን በፍርዷ ወንበር መካከል ጥብቅ አድርጌ፡ ምሳው ላይ ስላደርኩ፡ እንደምታውቁት፡ እ—እንደምታውቁት የቆየች ከፈይ ሱሪና፡ አነስ ያለች ሸሚዝ... ለብሼ ነበር። ስለዚህ በነጋታው ትንሿን ሸሚዝ ለብሼ፡ ወደ ጉባኤ ገባሁ። ገባሁና...

71 ከሦስት ዶላር በቀር ሌላ አልነበረኛም፡ ቤቴ ለመድረስ ነዳጅ መቅዳት ይገባኝ ነበር። ሌላ ደግሞ፡ የምታውቁት ዓይነት፡ የድሮ ሮል—ጥቂት ነበረኝ፡ ግን ደስተኛ ነበርኩ። ቦኖ ውሃ ወዳለበት ሄጄ፡ በብርጭቆ ውሃ እቀዳና፡ እንደምታውቁት፡ በጣም ደስ ይላሉ። እነሱን ውሃው ውስጥ አጥቅሼ አርሳቸውና፡ ቁርሴን እበላለሁ።

72 እነሱ፡ በቀን ሁለቴ ስለሚበሉ፡ አብሬ፡ ከእነርሱ ጋር መብላት እችል ነበር። ይሁን እንጂ በሚሰበሰበው ላይ አንዳች መስጠት ስላልቻልኩ፡ ተጠግቼ— እነርሱን ማስቸገር አልፈለግኩም።

73 እና በዚያ—በማለዳ ገባሁና፡ እንዲህ አሉ... ጥቂቱን ብቻ እናገራለሁ። ከዚያ በማለዳ ገባሁና፡ እንዲህ አሉ፡- “ትላንት ማታ፡ እዚህ መድረክ ላይ ከወጡት መካከል፡ ከባፕቲስት የሆነ፡ ወጣት ወንጌላዊ ዊልያም ብራንሃም ወደዚህ ይፈለጋል።” “የማለዳው መልዕክት እሱ እንዲሰብክ ፈልገናል፡” አሉ። ባፕቲስት ነኝ፡ በእነዚህ ሰዎች፡ የሚለቁኝ አይመስሉኝም። ወንበሬ ላይ ሸርተት ብየ ዝቅ አልኩ። እንደነገርኳችሁ እኛ ስንለብስ፡ እንደ ካህናት ነው፡ የለበስኩት ልብስ ግን ከፈይ ሱሪ እና ሸሚዝ ነው፡ ስለዚህ... እንዲህ ሆኜ ወንበሩ ላይ ቁጭ አልኩ። ከዚያ ሁለቴ ሶስቴ ተጣራ። ከአንድ ጥቁር ወንድም ጎን ነበርኩ።

74 ኮንቨንሽኑ በሰሜን ያደረጉበት ምክንያት፡ በደቡብ በኩል አድሎ እና መገለል ስለነበረ ነው። በዚህ ምክንያት ደቡብ ላይ ማድረግ አልቻሉም።

75 “ኢየሱስ ብቻ” ማለት ምን ማለት እንደሆነ ጥያቄ ፈጥሮብኛል። ይሁን እንጂ፡ “ኢየሱስ እስከተባለ ድረስ፡ ችግር የለም ብያለሁ። በዚህም ይሁን በዚያ... እርሱ ብቻ ይሁን እንጂ፡ ምንም ልዩነት አይፈጥርም።”

76 እና ባለሁበት ቁጭ ብየ እየኋቸው፡ ሁለት ጊዜ ሶስት ጊዜ ደጋግመው ጠሩ። ከጎኔ የነበረው ጥቁር ወንድም እየኝና፡ “ታውቀዋለህ’ዴ? ” አለኝ፤ እኔ— እ—እኔ... በቃ ፈተና ሆነብኝ። ሰውየውን መዋሸት አልፈለግኩም፡ መዋሸት አልፈልግምና።

ስለዚህ “ይሄውልህ ወንድም። አዎን፡ እኔ አውቀዋለሁ፡” አልኩት።

“ታዲያ፡ ሂድና ጥራዋ፡” አለኝ።

77 “አይ፡ ወንድሜ፡ እውነቱን—ልንገርህ፡” አልኩት፡ “ሰውየው እኔው ነኝ። ግን፡ እንደምታየኝ፡” “እየህ፡ ይሄን… ከፈይ ሱሪ ለብሼ፡” አልኩት።

“ተነሰና ሂድ።”

78 “አልፈልግም፡ እንዲህ ለብሼ አልሄድም፡” አልኩት፡ “እንዲህ ሆኜ፡ ይሄን ሱሪ፡ እና ሸሚዝ ለብሼ አልወጣም፡” አልኩት።

“እነዚህ ሰዎች አለባበስህ አያስጨንቃቸውም፡” አለኝ።

79 እኔም “ይሄውልህ፡ እዚህ፡ እንዳታጋልጠኝ፡ እሺ? ” አልኩት፤ “እየህ፡ እነዚህን የከፈይ ሱሪ ለብሼ፡ ወደ መድረክ መውጣት አልፈልግም፡” አልኩት።

“ዊልያም ብራንሃም ያለበትን የሚያውቅ ሰው አለ? ” አሉ፤

“እዚህ ነው! እዚህ አለ!” አላቸው፤

80 ኦህ፡ ማይ! ታውቃላችሁ፡ ፊቴ የምር ቀላ፤ ደግሞ፡ ከረባት ሳይኖረኝ፡ ትንሿን ሸሚዝ ለብሼ፡ ደግሞ፡ በዚህ ዓይነት እጅጌ። ጆሮዎቼ ግለው፡ እየተራመድኩ ደረስኩ። ማይክራፎን አጠገብም ቀርቤ አላውቅም።

81 እናም መሰበክ ጀመርኩ፡ በፍጹም የማይረሳኝ፡ “ባለጸጋው በገሃነም ሆኖ አይኖቹን አነሣና፡ አለቀሰ፡” የሚል አንድ ርዕሰ መረጥኩኝ። እኔ፣ ብዙ ጊዜ፣ እንደዚያ ያሉ ትናንሽ ባለ ሶስት አረፍተ ነገሮችን ብዙ ሰብኬአለሁ፦ “መጥታችሁ፡ ይህን ሰው እዩት፡” “ይሄን ታምኛለሽን? ” ወይም “ከዚያም አለቀሰ።” እና እንዲህ ማለት ጀመርኩ፦ “አበቦች የሉምና፡ አለቀሰ። የጸሎት ጉባኤዎች የሉምና፡ አለቀሰ። ልጆቹ የሉምና፡ አለቀሰ። መዝሙር የለምና፡ አለቀሰ።” አልኩኝና እኔም ራሴ አለቀስኩ።

82 ማይ፡ ካለቀ በኋላ፡ መጥተው፡ ሁሉም… በዙርያዬ ከበው፡ መጥቼ በጉባኤ እንድሰብክላቸው ይጋብዙኝ ጀመሩ። ስለራሴም፦ “ምናልባት እኔም ወንበር ሰባሪ ሳልሆን አልቀርም፡ አልኩ!” እያችሁ? “ምናልባት… ” እያችሁ፡ ደስ የሚሉ ሰዎች ናቸው።

83 ዞር ዞር አልኩ። የካው ቦይ ቡትስ፡ እና ትልቅ የካው ቦይ ኮፍያ ያጠለቀ፡ ሰው አግኝቼ “ማን ልበል? ” አልኩት፤

ከቴክሳስ “አገልጋይ **እከሌ-እና-እከሌ** እባላለሁ፡” አለኝ።

አሰብኩት፦ “እንዴ፡ እንዲህ እና እንዲያ ይመስላል… ”

84 ሌላም ወዳጅ ጎልፍ የሚጫውቱባቸው አይነቶች፡ እነሰ ያሉትን፡ ኒከር-ቦከር ዓይነት ሱሪ ለብሶ መጣ፡ አንደኛውም የጀርሲ ሹራብ ለብሶ መጣ። መጥቶም፦ “ከፍሎሪዳ አገልጋይ **እከሌ-እና-እከሌ** እባላለሁ። እባክህን መጥተህ ጉባኤ አገልግለን አለ… ”

85 እንዲህ አሰብኩ “ይገርማል፡ እቤቴ ነኝ እንዴ ያለሁት፡ ይሄን የከፈይ ሱሪ እና ሸሚዝ። ምንም ችግር የለውም።”

86 ስለዚህ፡ እነዚህን በተመለከተ እናንተም የህይወት ታሪኬን ሰምታችኋል፡ አሁን ግን እዚህ ጋር ላቁምና ከዚህ በፊት ያልነገርኳችሁ ነገር እንግራችኋለሁ።

አስቀድሜ ግን፡ ጥያቄ ልጠይቃችሁ... ልለፈው ብየ አስቤ ነበርና። ከዚህ በፊት፡ በህዝብ ፊት ይሄን ተናግሬው አላውቅምና። ይሄን ከመናገሬ በፊት እንደምትወዱኝ አድርጋችሁ እንደምትወዱኝ ቃል ከገባችሁልኝ፡ እጃችሁን ከፍ አድርጉልኝ። በጣም ጥሩ፡ ቃላችሁ ነው፡ ይሄን እንዳትረሱ።

87 በዚያ ምሽት በስብሰባው ላይ ተቀምጠው፡ ዝማሬዎችን ሲዘምሩ እጃቸውን ያጨበጭባሉ። "አውቃለሁ... " "ደሙ እንደሆነ አውቃለሁ። ደሙ እንደሆነ አውቃለሁ፡" የምትለዋን ትንሿ ዝማሬ፡ ይዘምሩ ነበር። መተላለፍያዎቹ ጋር ወደፊት ወድኋላ ይሮጣሉ፡ ጌታን እያመሰገኑ ይጮሃሉ፡ ወዘተ። "ይህ ነገር በጣም ይመስጣል፡" አልኩና። እኔም ጀመርኩ...

88 ከሐዋርያት ስራ ላይ፡ ሐዋርያት ስራ 2:4፣ ሐዋርያት ስራ2:38፣ ሐዋርያት ስራ 10:49፣ ሁሉንም ደጋግምመው ይጠቅሱ ነበር። "እንዴ፡ እንዴት ያለ ቃል ነው! ከዚህ በፊት በዚህ መልኩ ተረድቼው አላውቅም፡" ብየ አሰብኩ። ልቤ፡ አቤት፡ ተቀጣጥሏል፡ "ይህ ነገር ልዩ ነው!" አልኩኝ፤ መጀመሪያ ሳገኛቸው የቅዱሳን ወንበር ሰባሪዎች ሰብሰብ መሰለውኝ ነበር፣ "ኦህ፡ ማይ! አሁን ግን የመላዕክት ጉባኤ ናቸው፡" አልኩኝ። እያችሁ፡ ሐሳቤን በፍጥነት ቀየርኩት።

89 ስለዚህ በማግስቱ ጠዋት ጌታ እነዚህን ስብሰባዎች ለማድረግ ይህን ታላቅ እድል ሲሰጠኝ፣ እኔም፡- "ኦህ፡ ማይ፣ እኔ ከዚህ ህዝብ ጋር መቀጠል አለብኝ! 'ጯኺዎች ሜተዲስት፡' ተብለው ሲጠሩ የነበሩት እነዚህ ሳይሆኑ አይቀሩም።' እያልኩ ወደ ሌላ ሐሳብ ገባሁ፡" አሳብ ገባብኝ። "ምናልባትም እነሱ ሊሆኑ ይችላሉ።" "እኔ ብሆን፡ ወድጃቸዋለሁ... እርግጠኛ ነኝ። አቤት፡ የሆነ የወደድኩላቸው ነገር ነበር፡ ትሁታን እና ተወዳጆች ናቸው፡" አልኩኝ።

90 ቀልቤን የወሰደውና ያልገባኝ አንድ ነገር ነበር፡ በልሳን መናገር። እና... .አንድ ሰው **በዚያ** ማዶ፡ ሌላኛው ሰውዬ **በዚያ** ማዶ ቁጭ ብለዋል፡ እና፡ የስብሰባው መሪዎች ናቸው። **ይሄኛው** ተነስቶ በልሳን ይናገራል፡ **ያኛው** ይተረጉምለታል ስለ ስብሰባው እና ስለ ሌሎች ነገሮች ይናገራል፡ "ማይ፡ ይገርማል፡ ይሄን ነገር ማወቅ አለብኝ!" ብየ አሰብኩ። ደግሞም ይቀያየራሉ፡ **እዚህ** ላይ ይወርዳል እንደገናም **ወደዛኛው** ይመለሣል፤ ሁለቱም በልሳን ይናገራሉ፡ ይተረጉማሉ። ሌላው ማሕበር ሁሉ ይናገራል፡ ነገር ግን ሁለቱ ሰዎች በትርጉም እንደሚያመጡት እያክልም። አሁን፡ ሁለቱም አንድ ላይ ተቀምጠው አይቻቸዋለሁ፡ "አቤት፡ እነዚህ ሰዎች ግን፡ መላእክት መሆን አለባቸው!" ብየ እያሰብኩ፤ እዚያው ከኋላ በተቀመጥኩበት...

91 እናንተ (እንደምታውቁት) ጎትቼ ላመጣው የማልችለው ነገር፡ ወደ እኔ መጣ። ጌታ እንዳውቅ ከፈቀደልኝ፡ እንደምታውቁት፡ ነገሮችን የማውቅበት መንገድ አለ። ተናግሬው አላውቅም ያልኩት ነገር ይህ ነው፡ በህዝብ ፊት በፍጹም... ተናግሬው አላውቅም። አንዳች ነገር መመርመር ብፈልግ፡ ጌታ ራሱ ስለዚህ ነገር ሁሌ ይነግረኛል። ስጦታው የተሰጠበት ምክንያት ለዚህ ነው፡ እያችሁ። ስለዚህ እንደመጣልህ በሰዎች ላይ አይጣልም፡ እንዲህ'ማ ከሆነ ዕንቊህን በእርያዎች ፊት እንደመጣል ነው። ቅዱስ እና፡ ንጹሕ ነገር ስለሆነ፡ እንዲህ ማድረግ አይገባም። ካልሆነ ግን፡ ጌታ እኔንም ይጠይቀኛል። ለምሳሌ ከወንድሞች ወይም ከሌሎች ጋር ሰናወራ፡ የወንድሜን ስሕተት ለማወቅ ብየ መመርመር አልሞክርም።

92 አንድ ቀን ከአንድ ሰው ጋር ወንበር ላይ ቁጭ ብለናል፡ እና ሰውየው እጆቹን ትከሻዬ ላይ ጣል አርጎ፡ “ኦ፡ ወንድም ብራንሃም፡ እኔ’ኮ እወድሃለሁ፡” አለኝ። እና የሆነ የሚንቀሳቀስ ስሜት ተሰማኝ። እና ተመለከትኩት። ሊያታልለኝ አይችልም፡ እንደማይወደኝ አውቄዋለሁ፡ አያችሁ፡ ለምን ስለተጋለጠ ነው። አያችሁ፡ እጆቹን ትከሻዬ ላይ አርጓል፡ ግብዝ አለ ከተባለ፡ ፍጹም ግብዝ ማለት እሱ ነበር።

93 እኔም “እሺ፡ ይሁን፡” አልኩና፡ መንገዴን ሄድኩ። በዚያ መንገድ ላውቀው አልፈልግም። እኔ በፊት እንደማውቀው፡ እንደ ወንድም አውቄው፡ በዚያው ብቀጥል ይሻለኛል። ሌላው ግን ጌታ እራሱ ይመልከተው። ገብቷችኋል? እኔ እነዚህ ነገሮች ማወቅ... እነዚህን፡ ማወቅ አልፈልግም።

94 እና እነዚህ ነገሮች ላይ፡ ብዙ ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ አያጋጥመኝም። ቤት ቁጭ ባልኩበት፣ ሬስቶራንት ውስጥ በተቀመጥኩበት ቦታ፡ ወደ ፊት የሚሆን ነገር መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ ይነግረኛል። ይምለው ነገር እውነት እንደሆነ የሚያውቁ ሰዎች በዚህ አሉ። በቤቴ ውስጥ ቁጭ ብየ፦ “አሁን፡ ጥንቃቄ አድርጉ፡ ከአፍታ በኋላ የሚመጣ መኪና አለ። **እንዲህ-እንዲህ** የሚባል ሰው ነው። እንደምሚመጡ ጌታ ገልጦልኛልና፡ አስገቧቸው” እላለሁ። “ጎዳናው ላይ ስንወጣ፡ **እንዲህ** የሆነ ነገር ይሆናል። መስቀለኛው ጋር ስትደርስ ተጠንቀቅ፡ ልትጋጭ ትችላለህ።” አያችሁ፡ ሁሌም ቢሆን፡ እኔ እንዳልኩት፡ በትክክል ካልሆነ መርምሩ! ነገር ግን ሊያስጠይቃችሁ ስለሚችል፤ በዚያ ነገር ሙሉ ለሙሉ አትወሰዱ.... የእግዚአብሄር ስጦታ ስለሆነ፡ መጠቀም... ትችላላችሁ—አጠቃቀማችሁ ግን፡ መጠንቀቅ አለባችሁ። ካልሆነ ጌታ ይጠይቃችኋል።

95 ሙሴን እዩት፡ ሙሴ ከእግዚአብሔር-ዘንድ የተላከ ሰው ነበር። አስቀድሞ የተወሰነ፣ የተሾመ፣ እና ነብዪ ለመሆን የተሰራ! እንደሆነ ታምናላችሁ? እግዚአብሄር፡ አለቱን ምታው ካለው በኋላ፡ “ሂድና አለቱን ተናገረው፡” ብሎ አዞት ነበር። “ውሃን ያፈልቃልና፡ ሄደህ አለቱን ተናገረው፡” አለው።

96 ሙሴ ግን በቁጣ ወጣና፡ በፍጥነት ሄዶ፡ አለቱን መታ። ዉሃው ግን አልወጣም፡ “እናንተ አንገተ ደንዳኖች! ከዚህ አለት፡ ውሃን ልናፈልቅላችሁ አንችልምን? ” በማለት በድጋሚ መታው፤

97 እግዚአብሄር ያደረገው አይታችኋል? ዉሃው ፈለቀ፡ ይሁን እንጂ፡ “ሙሴ፡ ወደተራራው ውጣ፡” አለው። መጨረሻውም ያኔ ሆነ፡ አያችሁ። መለኮታዊ ስጦታዎችን፡ እንዴት እንደምትጠቀሙ... መጠንቀቅ አለባችሁ።

98 ሃይለኛ እና ጎበዝ ሰባኪ፡ ለመሰበክ ወጥቶ፡ መባና ገንዘብን ለመቃረም እንደሚሄድ፡ እግዚአብሔር ስለ ስራው ስራ ይጠይቀዋል። እውነት ነው። ስለመለኮታዊ ስጦታዎች ጥንቃቄ አድርግ። ወይም፡ አንዳንዶች፡ ታላቅ ዝና ለማትረፍ ወይም የቤተክርስትያንን ስም ለማስጠራት፣ ወይም ስማቸውን ለማግነን ይሰራሉ። እኔ ግን ሁለት ወይም ሶስት ምሽቶችን ጉባኤ አገልግዬ በሌላ ጉዳይ ተጠምጄ፡ ትሁት እና፡ የተዋረደ ብሆን እመርጣለሁ። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ይገባችኋል። አዎን፡ ወዳጄ፡ እግዚአብሄር እጁን ዘርግቶ አንተን ማግኘት በሚችልበት ስፍራ ተገኝ።

አስታውሱ፡ ይህ ማለት ውስጣዊ ህይወት ነው።

99 እና በዚያ ቀን፡ “እሺ፡ ወደ እነርሱ ልሂድና፡” ብየ አሰቤአለሁ። እንደው በነዚህ ሰዎች ተማርኬ ስለነበርኩ፡ “እስኪ እነዚህ ሰዎች ልመርምራቸው፡” ብየ አሰብኩ። እና ጉባኤው ካለቀ በኋላ ሰዎቹን ለማግኘት ጠበቅኳቸው። ዞር ዞር አልኩና። አንደኛውን አገኘሁት፡ “ጤና ይሰጥልኝ፡ ጌታዬ? ” አልኩት፤

100 እርሱም “ጤና ይስጥልኝ!” አለኝ፤ “ዛሬ ጠዋት የሰብከው ወጣት አንተ ነበርክ አይደል? ” አለኝ፤

ያኔ... ሀያ-ሶስት አመት ሆኖኝ ነበር። “አዎን፡ ጌታዬ፡” እኔ ነኝ አልኩት።

“ስምህ ማን ነበር? ” አለኝ፤

“ብራንሃም” እባላለሁ፤ “አንተስ? ” አልኩት፤

101 ሰሙን ነገረኝ። “አሁን መንፈሱ ጋር መነካካት በቻልኩ፡” እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ። እንዴት እንዴት እንደሆነ ለኔ ግልጽ አይደለም። “አልገባኝም፡ እንደው፡ ጌታዬ፡” አልኩት፡ “እናንተ እዚህ ያላችሁ ሰዎች ለእኔ የሌለኝ ነገር አላችሁ፡” አልኩት።

እሱም “ካመንክ ወዲህ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለሃል? ” ብሎ ጠየቀኝ፤

“አልገባኝም፡ እኔ ባፕቲስት ነኝ፡” አልኩት።

102 “ካመንክ ወዲህ ግን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለሃል ወይ? ” አለኝ፤

103 እኔም “ወንድሜ፡ አልገባኝም፡ ምን ማለትህ ነህ? ” አልኩት፤ “እኔ—እናንተ ጋር ያለው ሁሉ እንደአለኝ፡ ይሄን አውቃለሁ!” አልኩት። “ለየት ያለ ሃይለኛ የምሚመስል ነገር እንዳላችሁ ሰለምትመስሉ... ” ስለው፤

“በልሳን ተናግረህ ታውቃለህ? ” አለኝ፤

እኔም “ተናግሬ፡ አላውቅም፡” አልኩት።

“እኔ ቶሎ ልንገርህ መንፈስ ቅዱስ አልተሞላህም፡” አለኝ።

104 እኔም “መንፈስ ቅዱስ መሞላት... መለኪያው፡ ይህ ከሆነ፡ እንግዲያውስ አልተሞላሁም፡” አልኩት።

105 እሱም መለሰና “አዎን፡ ልሳን ካልተናገርክ፡ አልተሞላህም፡” አለኝ።

106 የተናገረውን እንዲሁ በመያዝ፦ “እሺ፡ የሚገኘውስ የት ነው? ” ብየ ጠየቅኩት፤

107 “ሂድ አንዱን ክፍል ውስጥ ግባና መንፈስ ቅዱስን ለምን፡” አለኝ።

108 እኔ ግን፡ እሱን መከታተሌን ቀጥያለው። እኔ ምን እያደርገኩ እንዳለሁ አላወቀም፡ እሱ እኔን ማየቱ በቀጠለ ቁጥር... ዓይኖቹ ሰበር ሰበር ብሏልና፡ እንግዳ ሰሜት እየተሰማው እንዳለ... እኔ ገብቶኛል። ነገር ግን... በትክክል ክርሰትያን ሆኖ አገኘሁት። የተጨበጨበለት፡ መቶ በመቶ፡ ፍጹም የሆነ ክርሰትያን ነው። በትክክል። በጣም ጥሩ፡ “ጌታ ይባረክ፡ ይሄውና! እኔ—እኔም—ልሂድና ያኛው መሰውያም ደግሞ ልፈልገው፡” አልኩ።

109 ሄድኩኝ፡ ዙርያውን ፈለግኩት፡ “ሌላኛውን ሰውየ ደግሞ አገኛለሁ፡” አልኩ። እንዳገኘሁትም መነጋገር ጀመርን፡ “ጤና ይስጥልኝ፡ ጌታዬ? ” አልኩት፤

110 እንዲህ አለኝ፦ “ንገረኝ እስኪ፡ የምን ቸርች አባል ነበርክ? ” “ባፕቲስት እንደሆንክ ነግረውኛል፡” አለኝ።

“ትክክል፡” አልኩት።

እርሱም “እስከ አሁን መንፈስ ቅዱስ አልተሞላህም፡ አይደል? ” አለኝ፤

እኔም “እንጃ እንግዲህ፡ እኔ አላውቅም፡” አልኩት።

“በልሳን ተናግረህ ታውቃለህ? ” ብሎ ጠየቀኝ፤

“አላውቅም፡ ጌታዬ፡” አልኩት።

“አይ አንተ አልተሞላህም፡” አለኝ።

111 “እንግዲህ፡ እናንተ ያላችሁ ነገር እንደሌለኝ አውቄአለሁ። ይሄን አውቃለሁ፡” አልኩት። “ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ ይሄን ለማግኘት እጅጉን ጓጉቻለሁ፡” አልኩት።

“ጥሩ፡ ማጥመቅያውም—እንደ ተዘጋጀ ነው፡” አለኝ።

112 “እኔ ተጠምቄአለሁ። ግን፡” “እናንተ ሁላችሁ ያላችሁ ነገር አልተቀበልኩም፡” አልኩት። “እኔ እንዲኖረኝ—የምመኘው ነገር እናንተ ጋር አለ፡” አልኩት።

“ጥሩ፡ ችግር የለውም፡” አለኝ።

113 አሁን ይሄኛው፡ ሁለተኛው ሰውዬ ነው፡ እና መንፈሱን ለመያዝ ሞከርኩ፡ እያችሁ። እና በ... በመጨረሻ ላይ ያዝኩት፡ በህይወቴ ከገጠሙኝ ርካሽና-ወራዳ ግብዞች፡ አንዱ እና ዋነኛው እሱ ነበር። ሚስቱ ጥቁር-ጸጉር ያላት ሴት ናት፡ የሚኖረው ግን... ወርቃማ ጸጉር ካላት ሴት ሁለት ልጆች ወልዶ አብሯት ይኖራል። ይሰክራል፣ ይሳደባል፣ መሸታ ቤት ይገባል፣ ብዙ ነገር ያደርጋል፤ ከዚህ ሁሉ ጋር ልሳን ይናገራል ይተነብያል።

114 በእውነት። “ጌታ ሆይ፡ ይቅር በለኝ፡” አልኩ። ወደ ቤቴም ሄድኩኝ። “እንጃ በቃ... ሊገባኝ አልቻለም። የተባረከው ቅዱሱ መንፈስ፡ እንዴት፡ በዚያ ግብዝ ሰው ሊወርድ ቻለ።” “በቃ፡ ሊሆን አይችልም!” አልኩኝ።

115 ከዚያ በኋላ ረዘም ላለ ጊዜ፡ እያለቀስኩ እና እያጠናሁ ቆየሁና፡ ምናልባት ከመካከላቸው አንዱን ባገኝ የዚህ ሁሉ ትርጉም ሊገባኝ ይችል ይሆናል ብየ አሰብኩ። አንደኛው፡ እውነተኛ ክርስትያን፤ ሌላኛው ግን፡ እውነተኛ ግብዝ ነው። አሳብ ገባብኝ፦ “ኦህ፡ ምን ይሆን? ” “ጌታ ሆይ፡ ምናልባት—ምናልባት እኔ ችግር ይኖርብኝ ይሆናል፡” አልኩ። ወግ አጥባቂ ከመሆኔ የተነሣ፡ እንዲህ አልኩ፦ “ይሄ ነገር... መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ማየት አለብኝ። መሆን አለበት።”

116 ለእኔ፡ የትኛውም አይነት ተግባር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻ ከሌለው ውሸት ነው። መነሻው ከዚህ መሆን አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ መረጋገጥ አለበት፡ አንድ ቦታ ብቻ ሳይሆን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ስፍራ መታየት አለበት። እኔ ላምነው ይገባኛል። እያንዳንዱ ነገር ከቅዱስ ቃል እጅ እና ጓንት ሆኖ ካልተያያዘ አላምነውም። ምክንያቱ ጳውሎስ ሲናገርም “መልዓክ ከሰማይ ወርዶ፡ የተለየ ወንጌል ቢሰብካችሁ፡ የተረገመ ይሁን፡” ብሎናልና። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ አምናለሁ።

“መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ አይነት ነገር በፍጹም ማየት አልቻልኩም፡” አልኩኝ።

117 ከሁለት አመታት በኋላ ግን፡ ሚስቴ እና ልጄን ካጣሁ በኋላ፡ በጥንታዊው፡ የጸሎት ሰፍራዬ፡ በግሪን ሚል በጸሎት ነበርኩ። ለሁለት ወይም ለሶስት ቀናት፡ ለሁለት ቀናት በዋሻው ቆየሁ። ጥቂት ትንፋሽ ለማግኘት፡ ልተንፍስ ብየ ወጣሁ። ልክ ሰወጣ፡ መጽሀፍ ቅዱሴ በመግቢያው አጠገብ ባለው የወደቀ ግንድ ጫፍ ላይ ተቀምጦ ነበር። ወድቆ የከረመ፡ የወጣ ጉቶ ያለው ዛፍ ነው። አሁን፡ ዛፉ **እንዲህ** ተጋድሞ ወድቋል... ወደላይ የወጣ ጉቶም አለው። ማታ ሲሆን እተኛበታለሁ፡ ግንዱ ላይ እግሮቼን ሰቅየ፡ ሰማይ ሰማዩን እንዲህ ብየ እያየሁ፤ እጆቼም **እንዲህ** ዘርግቼ፡ አንዳንዴማ እየጸለይኩ፡ ግንዱ ላይ ተዘርሬ እተኛለሁ። ምንም ሳልበላ ሳልጠጣ፡ እየጸለይኩ፡ ብዙ ቀናት እዚያው እቆያለሁ። እና ዋሻው ውሰጥ ይቀዘቅዛል፡ ይደነዝዛል፡ ሰለዚህ ንጹህ አየር ለመተንፈሰ፡ ከዋሻው ወጣሁ።

118 ከወጣሁ በኋላ መጽሀፍ ቅዱሴ ትላንትና ባሰቀመጥኩት ቦታ፡ ዕብራውያን 6ኛው ምዕራፍ፡ ተገልጦ አገኘሁት። “መጀመርያ የሚናገረው ትተን... ወደ... ወደ ፍጻሜ እንለፍ፡ ሰለ ሙት ሰራ ንሰሓ እና ሰለ እግዚአብሔር እምነት መሰረትን ደግመን አንመሰርት፡” ወዘተ የሚለውን ክፍል ማንበብ ጀመርኩ። “አንድ ጊዜ ብርሃን በርቶላቸው የነበሩትን፡ እንደገና ሰማያዊውን ጸጋ፡ እና የጥሪው ተካፋዮች ማድረግ የማይቻል ነው፡” ወዘተ። እንዲህ ይላል፦ “እሾህ እና ኩርንችትን ግን ብታወጣ ለመረገምም ትቀርባለች፤ መጨረሻዋም... ውሃ... ሊያዘጋጃት እና ሊያርሳት ዝናብ የምትጠጣ መሬት ለመረገምም—ለመረገም የቀረበች፡ እሾህ እና ኩርንችትን ግን ብታወጣ፡ መጨረሻዋ ትቃጠላለች ይላል።”

እና የሆነ ነገር “ውውውሽሽሽ!” ብሎ አለፈ፤

119 “መጣ። አሁን የሚለኝን እሰማለሁ... አሁን ራዕይ ሊያሳየኝ፡ ወደዚህ ጠርቶኛልና፡” ብየ አሰብኩ። ብግንዱ ጫፍ ሆኜ ጠበቅኩ፡ አሁንም ጠበቅኩ። ተነሣሁና ወደፊት ወደኋላ፣ ወደላይ እና ወደታች ዞር ዞር አልኩ። ተመልሼ መጣሁ፡ ምንም የለም። እንደገና ወደ ዋሻዬ ገባሁ፡ ምንም የለም። ከዚያ፡ ቆም አልኩና ማሰብ ጀመርኩ፦ “እንጃ፡ ምን ይሆን? ”

120 እንደገና ወደ መጽሐፍ ቅዱሴ ጠጋ አልኩ፡ እና፡ ኡህ፡ ሰውነቴ ሁሉ ወረረኝ። አነሳሁትና፡ “እንዳነብበው የፈለገኝ ነገር በውሰጡ ምን ቢኖር ነው? ” ብየ አሰብኩ፤ “ሰለ እግዚአብሔር ንሰሓ፣ እና እምነት፡” ወዘተ፡ የሚል ክፍል እሰከ ታች ድረሰ ማንበብ ቀጠልኩ፡ እንዲህ የሚል ክፍል ድረሰ አነበብኩ፦ “ብዙ ጊዜ በእርሰዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት፡ ለሚያርሷትም ደግሞ የምትጠቅም፤ እሾህ እና ኩርንችትን ግን ብታወጣ የተጣለች ናት መጨረሻዋም መቃጠል ነው።” እና፡ ኡህ፡የሆነ ነገር አንቀጠቀጠኝ!

121 ጌታ ሆይ፦ “ራዕይ ልታሳየኝ ነው፡ ወይሰ ሌላ አለ አልኩ... ” እኔ ሰለ ሌላ ጉዳይ ልጠይቀው ነበር የሄድኩት።

122 በቅጽበት፣ ምድር በፊቴ፡ ሲሽከረከር አየሁት፣ ሁሉም ታርሶ ተለሳልሷል። እነሆ ነጭ የለበሰ ሰው መጣ፡ እራሱን ቀና አርጎ፡ ዘርን እንዲህ ይዘራ ነበር። እርሱ ሲሄድ ግን፡ በመጣበት፡ በሸለቆው በኩል በሄደ ጊዜ፤ ከእርሱ በኋላ፡

ጥቁር የለበሰ ሌላ ሰው መጣና፡ እራሱን ወደ መሬት አቀርቅሮ፡ ዘር ዘራ። መልካም ዘሮች በበቀሉ ጊዜ፡ ስንዴ ሆነ፤ ክፉዎቹ ዘሮች በበቀሉ ጊዜ ግን እንክርዳዶች ሆኑ።

123 ከዚያም በምድር ላይ ታላቅ ድርቅ ሆነ፡ ስንዴውም ራሱን አቀረቀረ፡ ውኃን ፈልጎ፡ ሊጠፋ ተቃረበ። ከዚያ በኋላ ሰዎቹ ሁሉ እራሶቻቸውን ቀና ቀና አርገው፡ እግዚአብሄር ዝናብ እንዲሰድ መጸለይ ጀመሩ። ከዚያ እንክርዳዶቹን ተመለከትኳቸው፡ እራሳቸውን አቀርቅረዋል፡ ውሃን ፍለጋ ሰግደዋል። ወድያውም ታላቅ ደመና እንጣለለ ዝናብም በኃይል ወረደ። በወረደ ጊዜም፡ ጎብጠው የነበሩ ታናናሽ ስንዴዎች፡ "ዊሸሸሸ፡" ብለው ቀና አሉ። ከጎናቸው የነበሩ እንክርዳዶችም፡ "ዊሸሸሸ፡" ብለው ቀና አሉ።

"እንጃ፡ ምን ይሆን? " አልኩ።

124 እንዲህ ነው። አንድ ሐሳብ ወድያው መጣብኝ። ስንዴውን የሚያበቅለው ያው ዝናብ፤ እንክርዳዱንም ደግሞ ያበቅላል። በተሰበሰበው ህዝብ መካከል የሚወርደው መንፈሰ ቅዱስም፡ ሌላውን እንደሚባርክ ግብዞችም ሊባርክ ይችላል። ኢየሱስም "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፡" ብሏል። በመጮኹ፣ ወይም በመደሰቱ ሳይሆን፡ "በፍሬው ታውቁታላችሁ።"

125 "ይሄው ነው!" "ጌታ ሆይ፡ አሁን ገባኝ፡" አልኩት። የጸጋ ስጦታ ኖሮህ እግዚአብሔርን አለማወቅ ይቻላል። ሰውዬው... "የእውነታው ሐቅ ይህ ነው፡" አልኩት።

126 ከዚያ በኋላ፡ አያችሁ—ልሳን በመናገር ላይ ተቃዋሚ ሆኜ ነበር። አንድ ቀን ግን፡ እግዚአብሔር፡ አረጋግጦልኛል!

127 ጌታን ያስቀበልኳቸው የመጀመርያዎቹ ሰዎች፡ በኦሃዮ ወንዝ፡ በማጥመቅ ላይ ነበርኩ፡ የማጠምቀውን አስራ ሰባተኛው ሰው፡ ለማጥመቅ ሰጀምር፡ እንዲህ አልኩ፦ "አባት ሆይ፡ እኔ በውኃ አጠምቀዋለሁና፡ አንተ በመንፈሰ ቅዱስ አጥምቀው።" ብየ—እሱን ውኃው ውስጥ ማጥለቅ ጀመርኩ።

128 ወድያውም ከላይ ከሰማያት መንኰራኩር መጣ፡ ከዚያም ወደ ታች የሚያበራ ብርሃን ወረደ። ሰኔ ወር ነበር፡ ከሰዓት ሰምንት ሰዓት እናቱ ላይ፡ በመቶዎች እና መቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በወንዙ ዳር ቆመዋል። እኔ በነበርኩበት ቦታ ላይ መጥቶ ተንጠለጠለ። ድምጽም ከዚያ ወጥቶ፡ እንዲህ አለኝ፦ "መጥምቁ ዮኃንስ የመጀመርያውን መምጣቴ አዋጅ እንደነገረ፣ አንተም... የክርሰቶሰን ዳግም መምጣት የሚያውጅ መልዕክት ይኖርሃል አለኝ።" እና እስከ ሞት ድረስ ፈራሁ።

129 ከዚያ በኋላ ተመለሰኩ፡ በዚያ የነበሩ ሁሉ—የብረት ሰራተኞች እና ሌሎች፣ ባለ መድኃኒት ቤቶች፣ እና በወንዙ ዳር የነበሩ ሁሉ ተመልሰው ሄዱ። በዚያው ቀን ሁለት ወይም ሶስት መቶ የሚያህሉ ሰዎች አጠመቅኩ። ከውኃው ካወጡኝ በኋላ፡ ከውኃ ጎትተው ካወጡኝ በኋላ፡ ዲያቆናት እና ሌሎች፡ ቀርበው፦ "ብርሃኑ ምንድነው? ብለው ጠየቁኝ"

130 በአካባቢው የነበሩ—ከጊልት ኤጅ ባፕቲሰት ቤተክርሰትያን እና ሎን ሰታር ቤተክርሰትያን የሆኑ ከጥቁር ማሕበረሰብ፡ ብዙ ሰዎች በዚያ ነበሩ፡ የሆነውን ነገር አይተው ጮኹ፡ ብዙ ሰዎችም እራሳቸው ሰተው ወድቀዋል።

131 በቸርች ውስጥ የሰንበት ትምህርት አስተማሪ የነበረች፡ አንድ ሴት፡ የዋና ልብሷን ለብሳ ጀልባ ውስጥ ተቀምጣ ነበር፡ "ማርጂ፡ እንዴ ከዚህ ትወጪ? " ብየ ለማሰወጣት ሞከርኩ፤

እሷም "ቢሊ፡ ከዚህ መውጣት አይጠበቅብኝም፡" ብላ መለሰችልኝ።

132 እኔም አልኳት፦ "አዋን፡ አይጠበቅብሽም፡ ቢሆንም ግን ከማጠምቅበት አካባቢ መውጣትሽ ለወንጌሉ በቂ ክብር ሰላለኝ ነው።"

"አልወጣም፡" አለች።

133 በጥምቀት ሰለማታምን፡ ባለችበት ቁጭ ብላ፡ እኔ በማጥመቄ እያሾፈች እና እየተሳለቀች ቆየች፤ የእግዚአብሔር መልአክ በመጣ ጊዜ ግን ታንኳው ውስጥ በአፍ ጢሟ ተደፋች። ዛሬ ልጅቷ በአእምሮ ህሙማን ተቋም ውስጥ ገብታለች። አያችሁ? ከእግዚአብሔር ጋር አይቀለድም። ከዚያ፡ በኋላ... ከዚያ በኋላ፡ ቆንጆዋ ሴት መጠጥ ልትጠጣ ሄደች፡ በቢራ—ጠርሙዝ፡ በጠርሙዝ ተመታች፡ ፊቷ ተቆራረጠ። ኡህ፣ አሰፈሪ መልክ ያለው ሰው! እዚያ እንዲህ ተፈጸምባት።

134 ከዚያ በኋላ በህይወቴ ዘመን ሁሉ በተደጋጋሚ አያለሁ፡ ያንን እንቅሰቃሴ፣ እነዚያን ራዕዮች፣ ነገሮች እንዴት እንዴት እንደሚፈጸሙ አያለሁ። ከዚያ በኋላ፡ ጥቂት ቆይቶ፡ ያሰጨንቀኝ ጀመር፡ ሰው ሁሉ ስሕተት እንደሆነ ይናገረኛል። እናም ሁል ጊዜ ወደምጸልይባት፡ ወደ ተወደደች ቦታዬ ሄድኩ። ሄጄም... ይህ ነገር ዳግም ወደ እኔ እንዳይመጣ ብጸልይም፡ መምጣቱ ቀጠለ። እና ያኔ... በኢንዲያና ግዛት ውስጥ—የደን ጥበቃ—ባለሞያ ነኝ። መጥቼም፡ የቤተክርስትያናችን ፒያኖ ተጫዋች ሰው ወንድሙ፡ ቁጭ ብሎ አገኘሁት። እንዲህ አለኝ፦ "ቢሊ፡ እባክህ ዛሬ ከሰዓት ወደ ማዲሰን አብረኸኝ ትሄዳለህ? "

እኔም "አይ ወደ ጫካው መሄድ ሰለ አለብኝ፡ መሄድ አልችልም፡" አልኩት።

135 እና... ቤት ደርሼ ቀበቶዬን፣ የሽጉጥ ቀበቶዬን እና ነገሮችን አውልቄ፡ እጅጌዎቼን ወደላይ ሰብሰብ ማድረጌ ነበር። ምግብ ለመብላት እጆቼን ልታጠብ ተዘጋጀቼ፡ ያኔ ባለ ሁለት-ክፍል ትንሽ ቤት ውስጥ እንኖር ነበርን። ተጣጠብኩና፡ በቤታችን አጠገብ ባለው—ትልቅ ማፕል ዛፍ ስር፡ ወዲያ ወዲህ እየተንቀሳቀስኩ፡ ድንገት ቅጽበታዊ "ውውሽሽሽሽሽሽ!" የሚል ነገር መጣ፤ እንደ ሞተ ያህልም ሆንኩ። ዙርያዬን ቃኘውት፡ የተለመደው ነገር እንደሆነ አወቅኩ።

136 ደረጃዋቹ ላይ ቁጭ አልኩኝ፡ ከመኪናው ዘሎ ወጣና፡ ወደኔ እየሮጠ መጥቶ "ቢሊ፡ እራሰህን ሳትክ´ዴ? " አለኝ፤

"አይደለም፡ ጌታዬ፡" አልኩት።

"ቢሊ፡ ምንድነው የሆንከው? " አለኝ፣

137 እኔም "አላወቅኩም፡" አልኩት። "ደህና ነኝ፡ ወንድሜ፡ አመሰግናለሁ፡ አንተ ወደ ሰራህ ሂድ።" አልኩት።

138 ሚሰቴ ወጥታ አንድ ጆክ ውሃ አምጥታ፡ እንዲህ አለች፦ "ሀኒ፡ ምንድነው የሆንከው? "

“ምንም አልሆንኩም፡ የኔ ቆንጆ፡” አልኳት።

139 መጣችና፦ “በቃ አሁን ና፡ እራት ደርሷል፡” ይዛ ልታስገባኝ፡ እጆቿን በላዬ ላይ ጣል አረገች።

140 ሀኒዬ አልኳት፦ “እኔ፡ አንድ—የምነግርሽ ነገር አለኝ።” “ዛሬ ከሰዓት እንደማልመጣ ደውለሽ ንገሪአቸው፡” አልኳት። እንዲህ አልኳት፦ “ሜዳ፡ የኔ ቆንጆ፡” አልኳት፡ “በልቤ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምወድ እኔ አውቃለሁ። ከሞት ወደ ህይወት መሻገሬንም ይገባኛል። ይሁን እንጂ ዲያብሎስ እንዲጫወትብኝ አልፈቅድለትም።” “እንዲህ ሆኜ መቀጠል አልፈልግም፡ እስረኛ ሆኛለሁ፡” አልኳት። እንዲህ አልኳት፦ “ይህ ሁሉ ዘመን፡ እነዚህ ነገሮች ሁሉ፣ እና የመሳሰሉ ነገሮች፣ እና ራእዮች ሁሉ፣ ሌሎች ነገሮችም ሁሉ ተመላልሶብኛል። ወይም፡ እንጃ ምን እንደሆነ፡” “ብቻ ተመልሳልሶብኛል፡” አልኳት። ራእይ እንደሆነ ያኔ አላውቀውም። ራእይ አልለውም ነበር። “ቅዥት መሳይ ነገሮች፡” አልኳት፡ እና እንዲህ አልኳት፡ “ምንነቱን እኔ አላውቀውም። እና፡ ሀኒዬ፡ እ—እ—እ—እኔ ከዚህ ጋር መጃጃል አልፈልግም፡ ሰዎች ሁሉ—ዲያብሎስ ነው ብለውኛል። እኔ ጌታ ኢየሱስን እወደዋለሁ።”

141 “ተዋቸው፡” “ቢሊ፣ ሰዎች የሚነግሩህን ማዳመጥ የለብህም፡” አለችኝ።

142 “ግን፡ ሀኒ፡ ሌሎች ሰባኪዎችን ተመልከች፡” አልኳት። “አይ—እኔ አልፈልግም፡” አልኳት። “ጫካው ውስጥ ወደ ቦታዬ እሄዳለሁ። አስራ አምስት ዶላር አለኝ፣ ቢሊን አደራ፡” አልኳት። ቢሊ ያኔ ገና ጨቅላ ነበር፡ ገና ህጻን ልጅ ነበር። እንዲህ አልኳት፦ “ይሄን—ያዢና… አንቺ እና ቢሊን፡ የተወሰነ ጊዜ ያቆያችኋል። አንቺ ግን ደውዪላቸውና ምናልባት ነገ—ይመለሳል በያቸው፡ ለዘለአለምም ላልመለስ እችላለሁ። በሚቀጥሉ አምስት ቀናት ካለተመለስኩ፡ ባል አግብተሽ ኑሪ።” አልኳት፦ “ሜዳ፡ እግዚአብሔር ይሄን ነገር ከአንተ አንስቻለሁ እንደገና አይመጣብህም ብሎ ቃል እስከሚገባልኝ ድረስ ከጫካው በፍጹም አልወጣም።” የሰው ድንቁርና ምን ያህል እንደሆነ አስቡት!

143 እና በዚያ ሌሊት ወደዚያ ወጣሁ። መሸቶ ነበርና፡ ቀጣይ ቀን ከመሆኑ በፊት፡ ወደ ጎጆዋ ተመልሰኩ። በሚቀጥለው ቀን ወደማርፍባት ቦታዬ፡ ወደ ላይ… ተራራው፡ ወይም ገደል ጥግ፡ ለመሄድ አስቤአለሁና፡ በዚያ ባሉ ጫካዎች ለመውጣት አሰብኩ። ኤፍ.ቢ.አይ. በዚያ ያገኙኛል ብየ አላምንም። እና ይህች አሮጌ ጎጆ… ከመጨለሙ በፊት የከሰዓት ሙሉ ጊዜ በጸሎት አሳለፍኩት። “የነብያት መንፈስ ለነብያት ይገዛል፡” የሚለውን ቃል እያነበብኩ፡ ጸለይኩ። ምን ማለት እንደሆነ አልገባኝም። በዚያ አሮጌዋ ጎጆ እንዳለሁ ጨለመ።

144 ታዳጊ ሳለሁ አደን አጠምድበት ይህ ቦታ፡ ወጥመድ ነበረበት፡ ሄጄ አሳ እያጠመድኩ ሌሊቱን ሁሉ አሳልፋለሁ። ለብዙ ዓመታት፡ ወና ሆነ የቀረ ጎጆ ነው። አሁን የደረሰበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት ተከራይ የነበረበት ይመስላል።

145 እና በዚያ ሆኜ—ጠበቅኩት። እና “እንግዲህ፡” አልኩኝ። ማለዳ አንድ ሰዓት ሆነ፣ ሁለት ሰዓት፣ ሶሥት ሰዓት ሆነ፡ ወለሉ ላይ ወደ ታች ወደ ላይ እየተንቀሳቀስኩ ቆየሁ፡ ወደ ፊት ወደ ኋላ ተረማመድኩ። ያረጀች ትንሽ ኩርሲ ላይ ቁጭ አልኩኝ፣ ትንሽ… ኩርሲ ሳይሆን ትንሽ ሳጥን መሳይ ነገር። ተቀምጬም፦ “አምላክ ሆይ፣ ለምን እንዲህ ታደርግብኛለህ? ” ብየ

ማሰብ ጀመርኩ፤ "አባት ሆይ፡ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ። እንደምወድህ ታውቃለህ! የዲያብሎስ እስረኛ መሆን እ—እ—አልፈልግም። እነዚህ በእኔ ላይ መፈጸማቸው አልፈልግም። እባክህ አምላክ ሆይ፡ ከአሁን በኋላ እንዲመጡ ፈጽመህ አትፍቀድ፡" ብየ ጸለይሁ።

146 "እኔ—እወድሃለሁ። ገሀነም መውረድ አልፈልግም። እኔ ከተሳሳትኩ መሰበክ መሞከሬ፣ ጥረቴንም፣ ወደ ፊት ማውጣቴ ምን ይጠቅመኛል? እራሴን ብቻ ሳይሆን፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሌሎችን ወደ ገሀነም እየመራሁ ነው፡" አልኩ። በወቅቱ፡ ምናልባት፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ። እንዲሁም... ያኔ ሰፊ አገልግሎት ነበረኝ። "ከእንግዲህ፡ በእኔ ላይ—እንዲመጣ በፍጹም አልፈልግም፡" አልኩት።

147 እና በትንሿ ኩርሲ ቁጭ ብየ ነበር። ወደዚህ አቅጣጫ፡ ኦህ፡ **እንደዚህ** ብየ፡ ቁጭ ብያለሁ። እና፡ ቅጽበት፡ በክፍሉ ውስጥ ብልጭ ድርግም የሚል ብርሃን አየሁ። ላምባዲና የያዘ ሰው እየመጣ ይሆናል ብየ አሰብኩ። ዙርያዬን ቃኘሁ፡ "እንግዲህ... " እያልኩ ሳለሁ፤ ከፊት ለፊቴ፡ አየሁ። ከእንጨት የተሰሩ ያረጁ ጣውላዎች አሉ። ከፊት ለፊቴ፡ ተቀምጧል። በጥግ ደግሞ የተቀመጠ፡ እራሱ የተቀደደ ያረጀ የበርሜል ምድጃ ነበር። እና—እና **በዚያ** በአጠገቡ ወለሉ ጋር—ብርሀን ነበር፡ እና እኔም፦ "እንግዲህ፡ ከየት ይሆን? መቼም፡ እየመጣ አይነት አይደለም ብየ አሰብኩ... "

148 ዙርያየን አየሁ። **ይሄው** እራሱ ብርሃን፡ በላዬ ላይ ነበር፤ **እንዲህ** ከራሴ በላይ፡ ተንጠልጥሎ ነበር። ከእሱ በላይ፡ ኤመራልድ መልክ እንዳለው እሳት፡ እንዲህ "ዉሽሽሽ፣ ዉሽሽሽ፣ ዉሽሽሽ!" እያለ ይሄዳል፡ እንዲህ ይሽከረከራል። እና ተመለከትኩት። "ምንድነው? " ብየ አሰብኩ፡ አሁን፣ አሰፈራኝ።

149 ሰው ሲመጣ ሰማሁ፣ [ወንድም ብራንሃም የሚራመድን ሰው አስመሰለ—አርታዒ።] ዝም ብሎ፡ በባዶ እግሩ ብቻ፡ የሚራመድ ነበር። እና የሰው እግር ሲገባ አየሁ። ከላይ ወደታች የሚበራ ብርሃን ከነበረበት ቦታ በቀር፡ በክፍሉ ውስጥ ጨለማ ነው። እና የሰው እግር ሲገባ አየሁ። ወደ ክፍሉ በገባ ጊዜ፡ ሙሉ ለሙሉ ገባና፡ ሲታይም... ሁለት መቶ ፓውንድ የሚመዝን ሰው ይመስላል። እጆቹን **እንደዚህ** አጥፎአቸዋል። በፊት፡ በዐውሎ ነፋስ ውስጥ አይቼዋለሁ፣ ሲያናግረኝ ሰምቻለሁ፣ በብርሃን መልክም አይቼዋለሁ፣ ምሰሉን ግን ለመጀመሪያ ጊዜ አሁን አየሁት። እየተራመደም፡ ወደ እኔ እጅግ ተጠጋ።

150 እንግዲህ፡ ወዳጆች ሆይ፡ እንደው—ልቤ የምትከዳኝ መሰሎኝ ነበር። እንደው... አስቡት! እራሳችሁን በቦታው አስቀምጡ፡ ተመሳሳይ ስሜት ይሰማችኋል። ምናልባት ከእኔ በበለጠ ርቀት የተጓዛችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ፣ ምናልባትም የቆየ ክርስቲያን ልትሆኑ ትችላላችሁ፣ ምንም ቢሆን ግን ተመሳሳይ ስሜት ይሰማችኋል። ምክንያቱ ምክንያት ከመቶ እና በመቶዎች ከሚቆጠሩ ጉብኝቶች በኋላ፣ አሁንም እሱ ሲቀርበኝ ሽባ ያደርገኛል። እንዳንዴ'ማ... ፈጽሞ እንደ ሞተ ሰው እሆናለሁ፡ ብዙ ጊዜ ከመድረክ ሰወጣ በጣም እዳከማለሁ። ብዙ ከቆየሁ፡ ሙሉ በሙሉ እዝለፈለፋለሁ። የት እንዳለሁ እንኳ ሳላውቅ፡ ለሰዓታት እያሽከረክሩኝ ያጋጥመኛል። እና ልገልጸው አልችልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንብቡ እና ምን እንደሆነ ያብራራዋል። ቅዱሳት መጻሕፍትም ይመሰክራሉ!

151 ተቀምጬም እሱን ተመለከትኩት። እጆቼን—**እንዲህ** ወደ ላይ አንስቻለሁ። እሱም ደስ እንደሚል ነገር፡ እኔን ያየኝ ነበር። ድምጹም እውነተኛ ጥልቅ ነበር፡ እርሱም “አትፍራ፡ እኔ ከልዑል እግዚአብሔር ፊት ተልኬ መጥቻለሁ፡” አለኝ። ሲናገርም፡ ድምጹ፡ ከሁለት አመቴ ጀምሮ፡ የተናገረኝ ያ ድምጽ ነበር። እሱ መሆኑን አወቅኩት። እኔም ሀሳብ ገባብኝ፡ “አሁንስ... ”

152 አሁን ስሙት። ውይይቱን አድምጡት። ለማስታውስ ስለሚያስቸግረኝ፡ የቻልኩትን ያህል፡ የማውቀውን፡ ቃል በቃል ለመናገር እሞክራለሁ።

153 እኔ እሱን... እንዲህ ሳየው... እንዲህ አልኩት። እንዲህ አለኝ፡ “አትፍራ፡” ተረጋግቶ፤ እንዲህ አለኝ፦ “ስለ አስገራሚው አወላለድህ እንድነግርህ፤ ከልዑል እግዚአብሔር ፊት ተልኬ መጥቻለሁ... ” ልደቴ ምን እንደነበረ እንደምታውቁት ነው። እኔ ስወለድ ይህ ብርሃን በላዬ ላይ መጥቶ ነበርና። እና ሲናገር እንዲህ አለ፦ “ስለ አስገራሚው አወላለድህና ብዙዎች ያልተረዱት ህይወትህ ወደ ዓለም ሁሉ ሄደህ ለታመሙት ሰዎች እንድትጸልይላቸው እንደሚገባህ ያሳያል።” እንዲህ አለኝ፦ “ምንም ነገር ይኑርባቸው ብሎ... ” ለይቶ ተናገረኝ። እግዚአብሔር፡ ምስክሬ ነው፡ እርሱ ያውቃል። “ካንሠር፡” ብሎ ለይቶ ተናግሮኛል። እንዲህ አለኝ፦ “ስትጸልይ ትሁት ሆነህ; ሰዎች አንተን እንዲያምኑህ ካደረግካቸው... ምንም ነገር፣ ካንሠር እንኳን ቢሆን፡ ጸሎትህን ሊቋቋም የሚችል ምንም ነገር አይኖርም።” እያችሁ፡ “ሰዎች እንዲያምኑህ ካደረግክ።”

154 እና ጠላቴ ሳይሆን፡ ወዳጄ እንደሆነ አስተዋልኩ። እና እሱ ወደ እኔ ሲመጣ—እየሞትኩ ልሁን ወይስ ምን ልሁን ምን እንደሆነ አላውቅም ነበር። እኔም “እንግዲህ፡ ጌታዬ፡” አልኩት፤ “እኔ... ” ስለ ፈውስ እና ስለ እንደነዚህ ያሉ ስጦታዎች፡ ምንስ አውቃለሁ? አልኩት፤ “እንደው፡ ጌታዬ፡ እኔ'ኮ... እኔ—እኔ ድሀ ነኝ፡” አልኩት። “ከዘመዶቼ ጋር የምኖር ሰው ነኝ። የምኖረው ድሀ—ከሆኑት ቤተሰቦቼ ጋር ነው። አልተማርኩምም፡” ብየ መለስኩለት። “እና እ—እ—እኔ አልችልም፡ እነርሱም እኔን—አይረዱኝም፡” አልኩት። “እነሱ እኔን—በጭራሽ—እኔን አይሰሙኝም፡” አልኩት።

155 እርሱም እንዲህ አለኝ፦ “ነብዪ ሙሴ አገልግሎቱን በምስክር ለማጽናት ሁለት ምልክቶች፣ ስጦታዎች፣” ወይም፡ “አገልግሎቱን ለማጽናት፣ ሁለት ስጦታዎች እንደተሰጠው—አንተም አገልግሎትህን በምስክር ለማጽናት ሁለት ስጦታዎች ተሰጥቶሃል።” እንዲህ አልኝ፦ “አንደኛው አንተ የምትጸልይለት ሰው በእጅ ትይዘውና፡ ቀኝ እጁን በግራ እጅህ ትይዘውና፣” “ከዚያ ዝም ብለህ ጠብቀው፡ ከዚያ በኋላ... በሰውነትህ ላይ የሚፈጠር አካላዊ ለውጥ ታያለህ፡” አለኝ። “ከዚያ በኋላ ትጸልያለህ። ከለቀቀ፡ በሽታው ከሰዎቹ ለቋል ማለት ነው። ካልለቀቀ ግን፡ በረከትን ለምነህ አሳልፋቸው፡” አለኝ።

“እሺ፡” “ጌታዬ፡ የሚቀበሉኝ ግን አይመስለኝም፡” አልኩት።

156 እርሱም፦ “ሁለተኛው እንዲህ ይሆናል፡ አንደኛውን ካልሰሙት፡ ሁለተኛው ይሰሙታል።” “ሁለተኛውን በርግጥ ይሰሙታል።” ይህም፦ “እንዲህም ይሆናል በልባቸው የተሰወረ ምስጢር የምታውቅበት ጊዜ ይመጣል፡” አለኝ።

157 “እሺ፡” አልኩት፡ “ጌታዬ፡ ዛሬ ወደዚህ ሰፍራ የመጣሁት ለዚህ አላማ ነው። እነዚህ ወደ እኔ የሚመጡ ነገሮች ክፉ ነገሮች እንደሆኑ በብዙ አገልጋዮች ተነግሮኛል።”

158 እርሱም “ስለዚህም ምክንያት በዓለም ተወልደሃል፡” አለኝ። (እያችሁ፡ “ስጦታ እና ጥሪዎች አይጸጸትባቸውም።”) “በዚህ ዓለም የተወለድከው በዚህ ምክንያት ነው፡” አለኝ።

159 እኔም “እሺ፡ ጌታዬ፡” አልኩት፡ “ይህ ነገር፡ ቄሶቹ እንደነገሩኝ፣ እርኩስ መንፈስ ነው––ብለውኛል፡” አልኩት። “እዚህ... መጥቼ የምጸልየውም ለዚህ ነው፡” አልኩት።

160 እና እሱ ለእኔ የጠቀሰው ይህ ነው። ከጌታ ኢየሱስን የመጀመሪያ የመምጣት ጋር አያይዞ ነገረኝ። እኔም አልኩት...

161 ወዳጆቼ ሆይ፡ በጣም የሚገርመው ነገር... እዚህ ላይ፡ ለአንድ ደቂቃ ቆም ላርገውና፡ ወደ ኋላ ልመለስ። ከመቼውም ጊዜ በላይ ያስፈራራኝ የነበረው ነገር፡ ኮኮብ ቆጣሪዎች ባገኙኝ ቁጥር፡ አንድ ነገር እንደተፈጠረ ይረዳሉ። ይህም እኔን... እስከ ሞት ድረስ ያሰቸግረኝ ነበር።

162 ለምሳሌ፡ አንድ ቀን እኔ እና የአጎቶቼ ልጆች ወደ––ካርኒቫል አደባባይ እየሄድን፣ ያኔ ገና ታዳጊዎች ልጆች ነን፡ እና አብረን እየተጓዝን ነበርን። እናም አንዲት ኮከብ ቆጣሪ በአንዱ ድንኳን ውስጥ ተቀምጣ ነበር፣ ወጣት ሴት ናት፡ ቆንጆ-ውብ ወጣት እመቤት፡ ተቀምጣ ነበረች። እኛም ሁላችን፡ እየተራመድን ነን። ሴቲቱም፡ “አንተኛው፡ አንተ፡ አንዴ ና! አለች” እኛም ሶስት ወንዶች በአንድነት ዞርን። እርሰዋም፡ “አንተኛው ባለ እሰትራይፕ ሹራብ።” እኔን ጠራችኝ።

163 እኔም “አቤት እመቤት? ” አልኳት፤ ኮካ አምጣልኝ ልትለኝ ይሆናል፡ ወይም የሆነ ነገር ትልከኝ ይሆናል ብየ እሰቤ ነበር። እና እሷ ምናልባት–– በሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ የምትገኝ፡ ወጣት ሴት፡ ወይም የሆነ ነገር፡ እዚያ ተቀምጣ ነበር። እኔም ጠጋ ብየ፦ “አቤት፡ እመቤት፡ ምን ላምጣልሽ? አልኳት፤”

164 እርሰዋም “አንተን፡ የሚከተልህ––ብርሃን እንዳለ ታውቃለህ? የተወለድከው እንዲህ እና እንዲህ ምልክት ጋር ነው፡” አለችኝ።

“ምን ማለትሽ ነሽ? ” አልኳት፤

165 እሷም፦ “አንተ፡ የተወለድከው እንዲህ እና እንዲህ ምልክት ጋር ነው። አንተን የሚከተልህ ብርሃን አለ። ሰለ መለኰታዊ ጥሪ የተወለድክ ሰው ነህ አለችኝ።”

“ዞር በዪ፡ አንቺ ደግሞ!” ብያት፡

166 መንገዴን ቀጠልኩ፡ ምክንያቱ እናቴ እነዚህ ነገሮች የዲያብሎስ ናቸው ብላኛለችና። ትክክል ነበረች። ስለዚህ እኔ... በጣም ፈራሁ።

167 እና ሌላ ቀንም የደን ጠባቂ እያለሁ፣ ወደ አውቶብስ እየወጣሁ ነበር። አውቶቡስ ውስጥ ገባሁ። ሁሌም ለመናፍስት የተገዛሁ ያሰመስላል። እዚያ ቆሜ፡ እና አንድ ተጓዥ ከኋላዬ ቆሞዋል። ሄንሪ ቫይል ወደሚባል ጫካ፡ ለጥበቃ፡ በባስ ውስጥ፡ መንገድ ላይ ነበርኩ። በተደጋጋሚ እንግዳ ሰሜት እየተሰማኝ

ነበር። ዙሪያውን ቃኘሁ፡ እና እዚያም—አንዲት ወፍራም ሴት ቆንጆ ልብሰ ለብሳ፡ ቁጭ ብላለች። “ጤና ይሰጥልኝ? ” ስትለኝ፤

“ጤና ይሰጥልኝ!” አልኳት፤

168 እንደምታውቁት፡ እንዲሁ የምታወራኝ፡ ተራ ሴት ብቻ መሰላኝ ነበርና፡ ዝም አልኩ… “አንድ ደቂቃ ላናግርህ እፈልጋለሁ፡” አለችኝ።

እኔም፦ “እሺ፡ እመቤት? ” ብየ ዘወር አልኩ።

“የተወለድከው እንዲህ እና እንዲህ ምልክት ጋር እንደሆነ ታውቃለህን? ” አለችኝ፤

169 “ከእነዚያ ከንቱ ሴቶች አንዷ ናት፡” ብየ አሰብኳት። ስለዚህ ውጭ ውጭውን ማየቴን ቀጠልኩ። ቃል ትንፍሽ አላልኩም፡ ዝም አልኩ…

170 “አንድ ደቂቃ ላናግርህ እችላለሁ? ” አለች፤ ዝምታዬን ቀጠልኩ… እሷም “እንዲህ’ማ አትሁን፡” አለችኝ።

171 ፊት ለፊቴ ብቻ ማየት ቀጠልኩ። “ይህ ግን ጨዋነት አይደለም፡” ብየም አሰብኩ።

“ለአፍታ ብቻ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ፡” አለችኝ።

172 ፊት ለፊቴ ብቻ እያየሁ፡ ምንም አይነት አትኩሮት ሳልሰጣት ዝም አልኳት። ወድያውም “እንደሌሎቹ ተመሳሳይ ነገር ስትናገር እንደማያት እምናለሁ፡” ብየ አሰብኩ። ዘወር ሰል፡ ትዝ አለኝ፦ “ኦህ፡ ማይ! ይህ ነገር፡ እንደሚያስፈራኝ አውቀዋለሁ።” ማሰቡ በራሱ፡ ጠልቼዋለሁና። ዞርኩኝ።

173 “ምናልባት ማንነቴን ባስተዋውቅ ይሻላል፡” አለችኝ። “አስትሮሎጂስት ነኝ፡” አለችኝ።

“እንደነዚያ ዓይነት መሰለሽኝ ነበር፡” አልኳት።

174 “ባፕቲስት አገልጋይ የሆነ ልጄን ለመጠየቅ ወደ ቺካጎ እየሄድኩ ነው፡” አለችኝ።

“እሺ፡ እመቤት፡” አልኳት።

175 እሷም ጠየቀችኝ፦ “በምልክት ስር መወለድህን ነግሮህ የሚያውቅ ሰው አለ? ”

176 እያችሁ፡ ምን ልትለኝ ይሆን ብየ፡ ማየት ስለፈለግኩ… እኔም፦ “የለም፡ እመቤት፡” ብየ ዋሸኋት። ስትናገረኝም… “የለም፡ እመቤት፡” አልኳት።

እርሰዋም፡ “አገልጋዮች አልነገሩህም… ነግረውህስ አያውቁም? ”

“ከአገልጋዮች ጋር ምንም ህብረት የለኝም፡” አልኳት።

እርሰዋም “ኧረ-እህህ፡” አለች።

እኔም አልኳት… እሷም—አለችኝ… እንዲህ አልኳት፦ “እንግዲህ… ”

177 “በትክክል የተወለድክበትን ጊዜ ብነግርህ፡ ታምነኛለህ? ” አለችኝ፥

“አላምንሽም፡ እመቤት፡” አልኳት።

እርሰዋም “እኔ፡ መቼ እንደተወለድክ ልነግርህ እችላለሁ፡” አለችኝ።

“አላምንም፡” አልኳት።

178 እርስዋም “ሚያዝያ 6፡ 1909 ከጠዋቱ አምስት ሰዓት ላይ፡ ተወለድኩ፡” አለችኝ።

179 “ትክክል ነው፡” አልኳት።“እንዴት አወቅሽ? ” አልኳት፤ “እስኪ ካወቅሽ ይህ ተጓዥ መቼ እንደተወለደ ተናገሪ፡” አልኳት።

“አልችልም፡” አለች።

“ታዲያ እንዴት? እንዴት ልታውቂ ቻልሽ? ” አልኳት፤

180 “ይሄውልህ፡ ጌታዬ፡” አለችኝ። ስለ ከዋክብት አቆጣጠር መናገር ስትጀምር፡ እንዲህ አለችኝ፡ እሷም “በብዙ ዓመታት እንዴ... ” አለች፤ “የጥበብ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የመራቸው የንጋት ኮከብ ሲመጣ ታስታውሳለህ? ” አለች፤

181 ቆም አልኩና፡ ታውቂያለሽ፡ እኔ “ስለ ሐይማኖት ምንም ነገር አላውቅም፡” አልኳት።

182 እርሰዋም “ይሁን፡ ኢየሱስን ሊያዩ ስለመጡ ጠቢባን ግን ሰምተሃል፡” አለችኝ።

“አዎን፡” አልኳት።

እርሰዋም “እሺ፣ ጠቢብ ሰው ምን ነበር? ” ጠየቀችኝ፤

“ኦህ፡” “ጠቢባን ሰዎች እንደነበሩ፡ ብቻ አውቃለሁ፡” አልኳት።

183 እሷም አለችኝ፦ “ደህና፡ ጠቢብ ሰው ምን ነበሩ? ” “እንደ እኔ አይነት፡ አስትሮሎጂስት፣ ‘ኮኮብ ቆጣሪ’ ተብለው ይጠራሉ፡” አለችኝ። እንዲህ አለች፦ “እግዚአብሄር—በምድር ላይ አንዳች ነገር፡ ከማድረጉ በፊት፡ ሁልጊዜ በሰማይ እንደሚያሳይ፡ ከዚያ በኋላ በምድር እንደሆነ ታውቃለህ።”

“አላውቅም፡” አልኳት።

184 እና “እንግዲህ... ” አለች፤ ሁለት ወይም ሦስት፡ ሁለት... ሦስት ከዋክብት ጠራች፡ እንደ ማርስ፡ ጁፒተር፡ እና ቬኑስ ያሉ ሶስት ኮከቦች። እሷ እንዳለቻቸው ባይሆኑም “በምህዋራቸው ተገናኝተው አንድ ነገር ሰሩ... ” አለች፤ እሷም፦ “ጌታ ኢየሱስን ለማግኘት የመጡ ሦስት የጥበብ ሰዎች ነበሩ፣ አንደኛው ከሃም የዘር ሐረግ፣ እና ከሴም፣ ሌላኛውም ከያፌት ነበሩ።” እንዲህ አለች፦ “በቤተልሔም በተገናኙ ጊዜ፡ እነዚህ በምድር ከሚገኙ ሰዎች... ሁሉ የወጡ ሦስት ከዋክብት፡” “ከነዚያ ከዋክብት ጋር የሚያገናኛቸው አንዳች ነገር አላቸው፡” አለች። እሷም፦ “ያንን ተጓዥ ጠይቀው፡ ጨረቃ እና የሰማይ ፕላኔቶች ሲንቀሳቀሱ፡ ማዕበል አብሯቸው እንደማይሄድ እና እንደማይመለስ ጠይቀው አለችኝ።”

እኔም “እኔ እርሴ አውቀዋለሁ፡ እሱን መጠየቅ አያስፈልግም፡” አልኳት።

185 “እንጃ፡ የአንተ አወላለድ ግን ከከዋክብቶቹ ጋር የሚመሳሰል ነገር አለው፡” አለች።

“እንጃ፡ እኔ አላውቅም፡” አልኳት።

186 “እና፡ ሦስት ጥበበኞች ሰዎች መጡ፡” አለች። “እነዚህ ሦስት ከዋክብት፡ በመጡ ጊዜ... በተለያየ አቅጣጫ መጥተው በቤተልሔም ተገናኙ። ተነጋግረው ማረጋገጣቸው ይናገራሉ፡ አንዱ ከካም፣ ከሴም እና ከያፌት፣ ከሦስቱ

የኖህ ልጆች ዘር የመጡ ነበሩ።" አለች። "ከዚያ መጥተው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አመለኩ፡" አለች። "በተለያዩ ጊዜም፡" አለች፡ "ስጦታዎችን ሰጡን፡" አለችኝ።

187 "ኢየሱስ ክርስቶስም በአገልግሎት ዘመኑ ሲናገርም የመንግስቱን ወንጌል በዓለም ሁሉ (በካም፣ በሴም፣ እና በያፌት ዘንድ)፣ በተሰበከ ጊዜ ዳግም እመጣለሁ ብሎ ተናግሯል፡" አለችኝ። እና አለች፡- "እና አሁን፡ እነዚያን ፕላኔቶች፣ ማለት ሰማያዊ ፕላኔቶች፣ በተንቀሳቀሱ ጊዜ... " "ተለያዩ። ከዚያ ጊዜ በኋላ በምድር ታይተው፡ አያውቁም። ነገር ግን" አለችኝ፡- "በመቶ አመታት አንዴ **እንዲህ** ዙረታቸውን ይገናኛሉ፡" አለችኝ። ከዋክብት ቆጣሪ እዚህ ቢኖር ኖሮ፡ እሷ የምትናገረው ነገር ምን እንደሆነ ያውቃል። እኔ አይገባኝም። ስለዚህ ስትናገር-... "እንዲህ ይገናኛሉ፡" ብላለች። እና፡- "እግዚአብሔር ልጁን በሰጠ ጊዜ፡ ለሰዎች ልጆች ከተሰጠ ስጦታዎች ሁሉ የሚበልጠውን ስጦታ ለማሰብ ነው። እና፡ እነዚህን ፕላኔቶች በአንድነት ሲገናኙ" "ወደ ምድር ሌላ ስጦታ ይልካል፡" አለችኝ። እንዲህ አለችኝ፡- "አንተ የተወለድከው እነዚህ በሚገናኙበት ጊዜ ነው።" "እኔ ማወቅ የቻልኩበት ምክንያት ለዚህ ነው፡" አለችኝ።

188 በዚ፡ እሺ፡- "እመቤት፡ በመጀመርያ አልኳት፡ እኔ በፍጹም ይሄን አላምንም። የሐይማኖት ሰው አይደለሁም፡ በተጨማሪም ከዚህ በላይ ይሄን መስማት አልፈልግም!" አልኳትና ሄድኩ። በአጭሩ ቆረጥኩባት። መንገዴን ሄድኩ።

189 እና ሁሉ ጊዜ... እነርሱ በገጠሙኝ ቁጥር፡ የሚሆነው ይህ ነው። እና "ለምንድነው እነዚህ ዲያብሎሶች እንዲህ የሚያደርጉት? " ብየ እሰባለሁ፤

190 ሰባኪዎች ደግሞ፡ ሲናገሩ፡- "ይህ ከዲያብሎስ ነው! ዲያብሎስ ነው!" በማለት እንዳምናቸው አርገውኛል።

191 እና በዚያች ሌሊት... እርሱ ይሄን በጠቀሰልኝ ጊዜ፡ እንዲህ ብየ ጠየቅኩት፡- እንዲህ አልኩት፡- "እሺ፡ ጠንቋዮች እና ሌሎች ሁሉ፡ እና ዲያብሎስ ያደረባቸው ሰዎች፡ ሁልጊዜ ይሄን ይነግሩኛል፤ ወንድሞቼ የምላቸው፡ ቀሳውስት ግን፡ ከክፉ መንፈስ ነው እያሉ የሚናገሩት ለምንድነው? "

192 አሁን በሥዕሉ ላይ ተንጠልጥሎ ያለው እርሱ የተናገረውን አድምጡ። እርሱም "ያኔ እንደነበረው፡ አሁንም እንዲሁ ነው፡" አለኝ። እንዲህ በማለት፡ ይናገረኝ ጀመረ፡- "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት መውጣት በጀመረ ጊዜ፡ አገልጋዮች ሁሉ፡ 'ቡኤልዘቡብ፡ ዲያብሎስ ራሱ ነው' ብለውታል፤ ዲያብሎስ ራሱ ግን 'አንተ የእስራኤል ቅዱስ ነህ፡ የእግዚአብሄር ልጅ ነህ፡' ብሎታል አለኝ። አጋንንት... ጳውሎስ እና ባርናባስ በዚያ በሰበኩ ግዜ አስታውስ። አገልጋዮች ሁሉ፡ 'እነዚህ ሰዎች ክፉዎች ናቸው። ዓለምን ይገለባብጣሉ፡ እነዚህ ሰዎች—ዲያብሎስ ናቸው፡' አሉአቸው። አንዲት ኮኮብ-ቆጣሪ ግን በመንገድ ወጥታ ስለ ጳውሎስና በርናባስ የእግዚአብሔር ሰዎች እንደ ሆኑ አውቃ፡ እንዲህ አለች፡- 'እነዚህ ሰዎች የሕይወትን መንገድ የሚነግሩን የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው አለች።'" ልክ ነው አይደል? "መናፍስታውያን እና ሟርተኞች፣ አጋንንት-ያደረባቸው ሰዎች።"

193 ነገር ግን ስለ መንፈስ ምንም እስከማናውቅ ድረስ በሥነ መለኮት በጣም ተማርረናል። ከዚህ በኋላ እንደምትወዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ። እውነት እኮ

ነው። ማለቴ፡ ጴንጤቆስጣሎችም ጭምር! እውነት ነው። ስለጮኃችሁ እና ስለደነሳችሁ ብቻ ስለ መንፈስ ታውቃላችሁ ማለት አይደለም።

194 የግል ልምምድ ነው፡ ፊት ለፊት፡ እናንተም የሚያስፈልጋችሁ ይህ ነው። በአንድነት እና በኃይል፡ በመንፈስ በተሰበሰቡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ሊያስነሳት የፈለጋት ቤተክርስቲያን ይህች አይነት ናት፡ ልክ ነው።

195 የነገረኝም ይህ ነው። አገልግሎቱን እንዴት በስህተት እንደተረዱት ነገረኝ እና አገልግሎቱ በትክክል እንዳልተረዳሁት አረጋግጦልኛል። እና ስለ ኢየሱስ እና ስለዚህ ነገር ሁሉ ሲነግረኝ...

196 "እሺ ታዲያ፣ በእኔ ላይ የሚደርሱት፡ እነዚህ ነገሮችስ? " አልኩት፤

197 እና፡ እያችሁ፡ "እየበዛ እና እየበለጠ እና እየበለጠ ይሄዳል፡" አለኝ። ኢየሱስም እንዴት እንዳደረገ፡ እና መጥቶ፡ በጉድጓዱ አጠገብ የነበረች ሴት ህይወቷ የሚያውቅበትን ሐይል እንዴት እንደነበረው፡ እንዴት እንዲያደርግ አባቱ እንዳሳየው ማድረጉ ብቻ እንጂ፡ ፈዋሽ ነኝ አለምለቱን ነገረኝ።

"እሺ፡ ይህ ምን ዓይነት መንፈስ ነው? " ብየ ጠየቅኩት፤

እርሱም "መንፈስ ቅዱስ ነው፡" አለኝ።

198 ከዚያም አንድ ነገር በውስጤ ተፈጠረ፡ ጀርባዬን ያዞርኩበት ነገር እኔ እንድሰራው እግዚአብሔር እኔን ወደዚህ ያመጣበት ዋና ምክንያት እንደሆነ ተረዳሁ። እናም ጥንት እንደነበሩት ፈሪሳውያን ቅዱሳት መጻሕፍትን በተሳሳተ መንገድ እንደተረጎሙልኝ ተረዳሁ። ስለዚህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ የተናገረውን፡ የራሴን ትርጓሜ ወሰድኩ።

እኔም "እሄዳለሁ፡" አልኩት።

እርሱም "እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፡" አለኝ።

199 መልአኩም እንደገና ወደ ብርሃኑ ውስጥ ገባ በዙሪያው እና ዙሪያው፣ በዙሪያው እና ዙሪያው፣ እንዲህ ብሎ በእግሮቹ አካባቢ መምጣት መምጣት ጀመረ፡ ወደ ብርሃኑ በመሄድ ከሕንጻው ወጣ።

አዲስ ሰው ሆኜ ወደ ቤት ተመለስኩ።

200 ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ለሕዝቡ ሁሉ ነገርኳቸው። የ... እሁድ ምሽት ነበር።

201 ከዚያ እሮብ ማታ አንዲት ሴት ወደዚያ አመጡ፡ ከማዮስ ነርሶች አንዷ በካንሰር በሞት አፍ ደርሳ አመጧት፣ ጥላ ብቻ ቀርቷታል። እሷን ለመያዝ ወደ ታች ስሄድ፣ ወዲያው ራእይ መጣ፣ ወደ ነርስነቷ ስትመለስ እየኋት። "ለዓመታት አልቃ የነበረች፡" በሉዊስቪል ዝርዝር ውስጥ ትገኛለች። ለብዙ ዓመታት ነርስ ሆና በቆየችበት፡ በጄፈርስንቪል ውስጥ፡ ነርሲንግ እየሰራች አየኋት። ወደዚያ ተመልሼ፡ ያንን ራእይ፡ አይቻለሁና። እንደቆምኩ፡ የምሰራውን ሳላውቅ፡ ዞር አልኩ፣ መጀመሪያ እሷን አምጥተው በፊቴ ሲያኖሯት ደነገጥኩ። ነርሶች እና ሌሎች በዙሪያዋ ቆመው ነበር፡ ፊቷ ሁሉ ጎርጉዶ ዓይኖቿ ወደ ኋላ ገብተው፡ ተኝታ ነበር።

202 ማርጂ ሞርጋን። ደብዳቤ መጻፍ ከፈለጋችሁ፡ 411 ኮንብሎች ጎዳና፣ ጀፈርሰንቪል፣ ኢንድያና ነው። ወይም ወደ ክላርክ ካውንቲ ሆስፒታል ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና ጻፉላት። ምስክርነቱ—እሷ እራሷ ትነግራችኋለች።

203 እና ወደዚያ አየሁ። የመጀመሪያ ታማሚ ስተወጣ ለማየት፡ ወደዚያ ስመለከት፣ ራዕይ መጣ። ያቺ ሴት እንደገና ነርስ ሆና፡ ጥሩ እና ጠንካራ ጤናማም ሆና፡ ወዲያ ወዲህ ስትል አየኋት። እኔም "**ጌታ ስራዊት እንዲህ ይላል**፡ 'አትሞቺም በህይወት ትኖሪአለሽ!'" አልኳት፤

204 ባለቤቷ፡ በዓለም ባለጠግነት በጣም ከፍ ያለ ሰው፡ **እንደዚህ** አየኝ። "ሰውዬ፣ አትፍራ! ሚስትህ በህይወት ትኖራለች፡" አልኩት።

205 ወደ ውጭ ጠርቶ፡ ሁለት ወይም ሦስት ዶክተሮችን... ጠርቶ፡- "ታውቃቸዋለህ? " አለኝ፤

"አዎን፡" አልኩት።

206 "እንዴት፡" እኔ፡- "ከእሱ ጋር ጎልፍ ተጫውቻለሁ። 'ካንሰሩ አንጀቷ ላይ ተጠቅልሏል በኤነሚያ እንኳን ማጠብ አይቻልም፡'" አለኝ።

207 እኔ፡- "ምንም ይኑራት አይገደኝም! አንድ ነገር ግን አልኩት፡ እዚህ ራዕይ አይቻለሁ! ያየኸውን ሁሉ ተናገር፡ ያለኝ እርሱ፡ ተናገር እና፡ እንደተናገርከው ይሆናል ብሎኛል። እርሱም ነገሮኛል እኔም አምነዋለሁ።"

208 ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን! ከጥቂት ቀናት በኋላ ታጥቦላት፣ መዞር ጀመረች። አሁን ወደ አንድ መቶ ስልሳ አምስት ፓውንድ ትመዝናለች፣ ፍጹም ጤንነት ላይ ትገኛለች።

209 ከዚያም በተቀበልኩት ጊዜ፡ እየሰፋ ሄደ። ከዚያም ሮበርት ዳገርቲ ጋበዘኝ። እና እነሆ ሰፍቷል፡ በቴክሳስ በኩል፡ በመላው አለም ተሰፋፍቷል።

210 እና አንድ ምሽት፡ አራት ወይም አምስት ጊዜ ያህል... ያኔ በልሳን መናገር ወዘተ አይገቡኝም ነበር። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አምናለሁ፣ ሰዎች በልሳን መናገር እንደሚችሉ አምናለሁ። እና አንድ ምሽት... ሳን አንቶኒዮ፡ ቴክሳስ፡ ባለው ካቴድራል፡ እየተራመድኩ ወደ መድረክ ስወጣ፣ እዚህ ተቀምጦ የነበረ አንድ ወዳጅ እንደ ተኩስ ወይም እንደ ማሽን ሽጉጥ በፍጥነት በልሳኖች መናገር ጀመረ። ከኋላ፡ እዚያ ከኋላ፡ አንድ ሰው ተነስቶ **"ጌታ ሰራዊት እንዲህ ይላል!** አለ፤ ይህ ወደ መድረክ የሚሄደው ሰው ሁሉን በሚችለው አምላክ የተወሰነለትን አገልግሎት ይዞ እየገሰገሰ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት መንገድ ጠራጊ ሆኖ እንደ ተላከ። ይህ ሰውም በዳግም ምጽዓት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያስመጣ መልእክት አዘጋጅቷል።"

211 ጫማዬ ውስጥ መደበቅ ፈለግሁ። ቀና ብዬ ተመለከትኩና፡ "አንተኛው እሱን ታውቀዋለህ? " አልኩት፤

"አላውቀውም፡ ጌታዬ፡" አለኝ።

"አንተስ ታውቀዋለህ? " አልኩት፤

"አላውቀውም፡ ጌታዬ፡" አለኝ።

"እኔንስ ታውቀኛለህ? " አልኩት፤

"አላውቅህም፡ ጌታዬ፡" አለኝ።

“እዚህ ምን እያደረግክ ነው? ” አልኩት፤

212 እና... የሰብሰባው የመጀመሪያ ምሽት ነበር። “ጋዜጣ ላይ አንብቤ ነው፡” አለኝ።

ወዲያኛው አየሁና “አንተስ እንዴት ወደዚህ መጣህ? ” አልኩት፤

213 “አንዳንድ ዘመዶቼ ‘መልኩታዊ ፈዋሹ’ እዚህ ይመጣል ብለውኝ፤ መጣሁ፡” አለኝ።

“ሁለታችሁም አትተዋወቁም? ” አልኩት፤

“አንተዋወቅም፡” አለኝ።

214 ኦህ፡ ማይ! ለመጀመርያ ጊዜ በዚያ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል አየሁ... ምንም እንኳን ባውቀውም፡ ያኔ እኔ ስህተት ነው ብዬ አሰበው የነበረውን... እነዚያን ነገሮች ካላቸው ሰዎች ጋር የነበረው እርሱ የእግዚአብሔር መልአክ እራሱ ነበር። ምንም እንኳን በመካከላቸው ብዙ ግብዞች ብዙ-ድብልቅ እና ብዙ ጩኸት የነበራቸው ቢሆኑም፣ በመካከላቸው ግን እውነተኛ ህይወት ነበረች። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—እርታዒ።]... ክርስቶስ ነበረ። እውነት—እንደሆነም አይቻለሁ።

215 ኦህ፡ ብዙ ዓመታት አለፉ፡ በየጉባኤዎቹ ሰዎች ራእዮችን ያያሉ፡ ብዙ ነገሮችም ይሆኑ ነበር።

216 አንድ ጊዜ በአርካንሳስ በነበርኩ ጊዜ፡ እንዲህ አይነት ጉባኤ ውስጥ ይመስለኛል፡ አዳራሹም ተመሳሳይ ቦታ ላይ፡ ቆሜ ፎቶግራፍ አንሺ ቀርጾታል። እና ቆሜ፡ ለማስረዳት እየሞከርኩ ነበር። ብዙ ሰዎች፡ ከሜተዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ እና ፕረሰቢተርያኖች፡ ሁሉ፡ አውቀውት ተቀምጠው ያዳምጡ ነበር። እናም በአጋጣሚ፡ በበሩ አጠገብ ሲመጣ፡ “ዉሽሽሽ፡ ውሽሽሽ!” እያለ የሚሄድ እና የሚመጣ፡ ነገር አየሁ፡

217 እኔም “ከአሁን በኋላ እርሱ ስለመጣ፡ እኔ መናገር አይገባኝም፡” አልኳቸው። እየጨመረ መጣ፡ ከዚያ ሰዎች ሁሉ ዋይ ዋይ ማለት ጀመሩ። እኔ ወዳለሁበት ቦታ ደርሶ ቆመ።

218 መቆም እንደጀመረ፡ አንድ አገልጋይ እየሮጠ መጥቶ፡- “አየሁት፡ ይታየኛል አለ!” ማየት እስኪሳነው ድረስ መታው—እየተንገዳገደ፡ ወደ ኋላ ተመለሰ። አንገቱን አቀርቅሮ እየተንገዳገደ ወደ ኋላ ሲመለስ እዚያው በመጽሐፉ ውስጥ አይታችሁ። ምስሉን ማየት ትችላላችሁ።

219 እና ወርዶ ቆመ። በዚያ ጊዜ የጋዜጣው ፎቶግራፍ አንሺ ቀርጾታል። ያኔ ግን የጌታ ጊዜ አልነበረም።

220 እና ሌላው በሂዩስተን፣ ቴክሳስ፣ ኦህ፣ በሺዎች ጊዜ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች፡ በነበሩ ጊዜ... ከሰምንት መቶ... ከሰምንት ሺህ በላይ ህዝብ ሰሙ-ማን-ነበር-ወደ ሚባለው፣ ወደ ሙዚቃው አዳራሽ፣ ወደ ታላቁ ሳም ሂውስተን ኮሊሲየም ገባን።

221 እና በዚያ ምሽት በዚያ ክርክር ውስጥ፣ አንድ የባፕቲስት ሰባኪ ስለ እኔ ይናገር ነበር “ተራ-ግብዝ እና አስመሳይ፣ ከሃይማኖት አስመሳይነት የዘለለ

ምንም ነገር እንደሌለኝ፣ ከተማውን ለቅቄ መውጣት እንዳለብኝ” ይህንም ማድረግ ያለበት እርሱ እንደሆነ ይናገር ነበር።

222 ወንድም ቦሰዋርዝም፦ “ወንድም ብራንሃም ይህ እንዲሆን ዝም ትላለህን? ግባ እና ግጠመው እንጂ! አለኝ”

223 እኔም “አይሆንም፡ ጌታዬ፡ እኔ በመሰዳደብ አላምንም። ወንጌል እንድንኖረው እንጂ ለስድብ አልተሰጠንም፡” አልኩት። “ምንም ያህል ብታሳምነው፡ አካሄዱን ፈጽሞ አይቀይርም፡” ብየ መለስኩለት። “ለእሱ... ምንም ለውጥ አያመጣለትም። እግዚአብሔር ለልቡ መናገር ካልቻለ፣ እኔ እንዴት እችላለሁ? ” አልኩት፤

224 በሁለተኛው ቀን ሂውሰተን ክሮኒክል፦ “ከምን እንደተፈጠሩ ያሳያል፡” የሚል ጽሑፍ ይዞ፡ በድጋሚ ወጣ። “ስለሚያስተምሩት ነገር አቋም ለመያዝ ፈርተዋል፡ ይህም ከምን እንደተፈጠሩና ማን እንደሆኑ ያሳያል፡” ይላል።

225 የተወደደው ሽማግሌ ወንድማችን ቦሰዋርዝ፡ ያኔ በሰባዎቹ ዕድሜው ውስጥ ነበር፡ እና ወደ እኔ መጣ፣ እጁን በእኔ ላይ አድርጎ፦ “ወንድም ብራንሃም፡” አለኝ፡ “ልትገጥመው አትሄድም ማለት ነው? ”

226 “አልሄድም፡ ወንድም ቦሰዋርዝ። አልሄድም ጌታዬ። እኔ ለመግጠም አልሄድም።” “ምንም አይጠቅምም፡” አልኩት። “ከመድረክ ሰንወጣ መሰዳደብን ይፈጥራል፡” አልኩት። “አሁን ጉባኤ ላደርግ ስለሆነ፣ ነገሮች እንደዋዛ እንዲበላሹ አልፈልግም፡” አልኩት። “ዝም በለው ይቀጥል፡” አልኩት። “ተወው፡ ይፍጨርጨር፡” አልኩት። “ከዚህ በፊት ብዙዎች ገጥመውናል፡ ከእነዚህ ጋር መነጋገር ምንም ጥቅም የለውም፡” አልኩት። “እንደ አመጣጣቸው፡ ወዲያውኑ ይመለሣሉ፡” አልኩት። እንዲህ አልኩት፦ “አንድ ጊዜ የእውነትን እውቀት ሰምተው ባይቀበሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ቀይ መሰመሩን ያልፋታል ይላቸዋል በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ይቅርታ እንደማይደረግላቸው ተናግሯል። ‘ዲያብሎስ’ ብለው ይጠሩታል እንጂ አይቀበሉትም። ከዚያ በሃይማኖት መንፈስ ማለት በዲያብሎስ ይሞላሉ።”

227 የዲያብሎስ መንፈስ በትክክል ሃይማኖተኛ መሆኑ፡ ሰንቶች ታውቃላችሁ? አዎን፡ ወዳጆች ሆይ፡ የቻሉትን ያህል አክራሪዎች ናቸው። ምናልባት፡ አሁን “አክራሪዎች፡” ማለቴ ጥሩ ባይመስልም፡ እውነት ነው። “የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል።” ትክክል። የእግዚአብሔር ነገር የሚረጋገጠው ሁልጊዜ በምልክቶችና በድንቆች ነው። በመጨረሻው ቀንም ይህ ነገር እንደሚሆን ተናግሯል። እና ልብ በሉ!

228 ሽማግሌው ወንድማችን ቦሰዋርዝ፡ ገና... ከጃፓን መምጣቱ ነው፡ እና ደካክሞታል። ከእኔ ጋር መምጣት ነበረበት። እዚህ መምጣት ፈልጎ ነበር። በሉቦክ ግን ከእኔ ጋር ይገኛል። አሁን ትንሽ... መጥፎ ጉንፋን፡ ስለታመመ፡ እሱ እና ሚስቱ፡ አሁን ላይ መምጣት አልቻሉም። እና እሱን...

229 ሁሉም ካሌብ ይመስላል ብለው አሰቡ። እንደምታውቁት፡ በዚያ በተከበረ ቁመናው፡ ቆሞ፦ “ይሁን፡ ወንድም ብራንሃም፡” አለኝ፦ “አንተ አልሄድም፡” ካልከኝ፡ “እኔ ልሂድ ልጋፈጣቸው፡” አለኝ።

230 “ወንድም ቦሰዋርዝ፣ እኔ—እንድትሄድ አልፈልግም። ለመሰዳደብ ትሄዳለህ፡” አልኩት።

“እንድም ክፉ ቃል አይኖርም፡” አለኝ።

231 አሁን፡ ከመዝጋቴ በፊት፡ ይሄን ሰሙት። “ምንም አይነት ክፉ ቃል ካልተናገርክ፡ ችግር የለውም፡” አልኩት። ወድያው ሄደ።

“እንዳልከራከር ቃል እገባለሁ፡” አለኝ።

232 በዚያ ምሽት ወደ ሰላሳ ሺህ የሚጠጉ ሰዎች በአዳራሹ ተሰብሰበው ነበር። ወንድም ዉድ፡ አሁን እዚያ ጋር የተቀመጠው፡ በዚያን ጊዜ በአዳራሽ ውስጥ ተቀምጦ ነበር። እኔ ደግሞ...

233 ልጄ እንዲህ አለኝ፡ ማለቴ... ባለቤቴም “ወደ ሰብሰባው አትወርድም’ዴ? ” አለችኝ፤

234 “አልሄድም። ክርክር ለመሰማት ብዬ ወደዚያ አልሄድም። በጭራሽ፡ አላረገውም። እዚያ ድረስ ሄጄ ይሄን አልሰማም፡” አልኳት።

አመሻሽ ላይ፡ አንድ ነገር፡ “እንዲሄድ አዘዘኝና።”

235 ታክሲ ጠርቼ፡ ከወንድሜ፣ እና ሚስቴ እና ልጆቼ ጋር ሆነን፡ ወደዚያ አመራን። እንደዚህ ወደ ላይ ከፍ ወዳለው፡ ሰላሳኛው ባልኮኒ ላይ ወጥቼ፡ ቁጭ አልኩ።

236 ታውቃላችሁ፡ ሽማግሌው ወንድም ቦሰዋርዝ እንደ ዲፕሎማት ወጣ። ኮፒ ያደረጋቸው ነገሮች ይዞ... ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጡ ሰድሰት መቶ የሚያህሉ የተላዩ ተሰፋ ቃሎችን ይዞ ነበር። እርሱም፡- “ዶክተር ቤሰት ሆይ፡ አሁን፡ ወደዚህ መጥተህ ከእነዚህ ተሰፋዎች ውስጥ አንዱን ወሰደህ በመፅሃፍ ቅዱስ ሰህተቱን አሰረዳን። ኢየሱስ ክርሰቶስ በዚህ ዘመን ህመምተኞችን እንደሚፈውሰ የሚያሳዩ፡ እነዚህ ተሰፋዎች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው። ከእነዚህ ተሰፋዎች አንዱን ወሰደህ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ ከመጽሐፍ ቅዱሰ ጋር ማቃረን ከቻልክ፡ እጅህን ጨብጬ፡ ‘ትክክል ነህ፡’ ብየህ፦ ቁጭ እላለሁ አለው።:”

237 እርሱም “ወደ መድረክ ሰወጣ አሳይሃለሁ!” ብሎ መለሰለት፤ ወንድም ቦሰዋርዝን ማጣጣል እንዲመቸው የመጨረሻውን ፈለገ፡ አያችሁ።

238 ሰለዚህ ወንድም ቦሰዋርዝ እንዲህ አለ፦ “እሺ፡ ወንድም ቤሰት፡ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ፡ አንተም ‘አዎን’ ወይም ‘አይደለም፡’ ብለህ ከመለሰክልኝ “ክርክሩን አሁን እናቆመዋለን፡” አለው።

እርሱም “ሰወጣ አሳይሃለሁ!” ብሎ—መለሰለት፤

አወያዩን ሊጠይቀው ይችል እንደሆነ ጠየቀው። “ይቻላል፡” አለው።

239 እንዲህ ብሎ ጠየቀው፦ “ወንድም ቤሰት፡ የጆሆቫ የመቤዠት ሰሞች ኢየሱስ ተጠርቶባቸዋል አልተጠራባቸውም? ‘አዎን’ ወይስ ‘አይደለም’? ”

240 በቃ ደመደመው። በቃ እርፍ። ምን ልበላችሁ፡ የሆነ ነገር በውስጤ ሲፈሰ ተሰማኝ። አያችሁ፡ እኔ ራሴ፡ አሰቤው አላውቅም። “ኦህ፡ ማይ፡ ይሄን አይመልሰውም! ቊልፉ ይህ ነው፡” እያልኩ ማሰብ ጀመርኩ።

“እየህ፡ ዶክተር ቤሰት፡ እኔ—እኔም ተገርሜአለሁ፡” አለው።

እርሱም “መጥቼ እመልስልሃለሁ!” አለው፤

241 “የደከመውን ጥያቄዬን መመለስ ባለመቻልህ ገርሞኛል፡” ብሎ ተናገረው። ያመነውን እንደሚያውቅ ሰው፡ እንደ ዱባ ጸና። ከዚያ በኋላ ያቺን ቅዱስ ቃል ነክሶ ተቀመጠ።

“ሠላሳ ደቂቃዎችህን ውሰድና፡ ከዚያ በኋላ እመልሳለሁ!” አለው፤

242 ሽማግሌው ወንድም ቦስዋርዝ ያቺን ቃል ይዞ ቁጭ አለና የሰውየው ፊት ክብሪት እስኪለኰሰበት ድረስ ቀልቶ፡ በዚያ ሁኔታ አሰሮ ያዘው።

243 የያዛቸውን ወረቀቶች ሁሉ ወለሉ ላይ በትኖ፡ ከመቀመጫው፡ በቁጣ ተነሣ፡ ወደ መድረኩ ወጣና ጥሩ የካምቤላይቶች ሰበከት ሰበከ። እኔ እራሴ ባፕቲስት ስለነበርኩ፡ የሚያምኑትን አውቀዋለሁ። “‘የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ፡’ ያኔ መለኰታዊ ፈውስ ይሆንልናል፡” በማለት… ትንሳኤን እየሰበከ ነበር። ኦህ፡ ማይ! የማንሞት ከሆንን በኋላ መለኰታዊ ፈውስ ምን ይጠቅመናል (“የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ፡” የሙታን ትንሣኤ)? ኢየሱስ አልዓዛር ላይ የሰራውን ታምራትም አላመነበትም፡- “ድጋሚ ሞቷል፡ ጊዜአዊ ነገር ነው፡” በማለት አሾፈበት። አያችሁ?

244 ይሄን ሁሉ ካደረገ በኋላ፡ “መለኰታዊ ፈዋሹን አምጡልኝና ሲፈውስ ልየው!” ማለት ጀመረ፤

245 ከዚያ በኋላ ትንሽ ምልልስ ሆነ። ወንድም ቦስዋርዝም ተናገረ “እኔ የገረምከኝ፡ ወንድም ቤሰት፡ የጠየቅኩህን ጥያቄ አንድ አለመመለስህ ነው፡” አለው።

246 ይህን ባለው ጊዜም ተበሳጨና፡ “መለኰታዊ ፈዋሹን አምጡልኝና ሲፈውስ ልየው!” አለ፤

“ወንድም ቤሰት፡ ሰዎች እንደሚድኑ ታምናለህ? ” በማለት ጠየቀው፤

“አዎን!” ብሎ መለሰ፤

እርሱም “ታዲያ መለኰታዊ አዳኝ ብለው እንዲጠሩህ ትፈልጋለህን? ” አለው፤

“በፍጹም አልፈልግም!” ብሎ መለሰ፤

247 “አዎን… ስለ ነፍስ መዳን ስለሰበክህ መለኰታዊ አዳኝ አያደርግህም።”

“አዎን፡ እንድሆን አያደርገኝም!” አለ፤

248 አለውም፡- “ወንድም ብራንሃምም የስጋን ፈውስ ስለሰበከ መለኰታዊ ፈውስ ፈዋሽ አያደርገውም። መለኰታዊ ፈዋሽ አይደለም፡ ሰዎችን ግን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል።”

249 እርሱ ግን፡- “አምጡት ወደዚህ፡ ተአምር ሲያደርግ ልየው! ከዚያ በኋላ ሰዎቹን፡ የዛሬ አንድ አመት ልያቸውና፡ ማመኔን አለማመኔን እነግራችኋለሁ።”

250 ወንድም ቦስዋርዝ እንዲህ አለው፡- “ወንድም ቤሰት፡ ነገርህ የቀራንዮን ነገር በድጋሚ መፈጸም ይመስላል፡ ‘ከመስቀል ላይ ውረድ እኛም እናምንሃለን አስመስልከው’ኮ።” አያችሁ?

251 ከዚያ በኋላ፡ አቤት፡ በጣም ተቆጣ። እንዲህም አለ፦ “ሲሰራ ልየው! ሲሰራ ልየው!” አወያዮቹም ቁጭ እንዲል አደረጉት። እዚያ አጠገብ ቆሞ ወደ ነበረው ጴጤቆስጤ ሰባኪ፡ ጠጋ አለና፡ መድረኩ አቋርጦ ደበደበው። ወድያው አስቆሙት። (ወንድም ቦሰዋርዝም “እዚህ፣ እዚህ! አይደለም፡ አይደለም፡” አለ።) ከዚያ አወያዮቹ ቁጭ እንዲል አደረጉት።

252 ሬይመንድ ሪቼ ተነሰቶ፦ “የደቡብ ባፕቲሰት ኮንቬንሽን አመለካከት ይህ ነውን? ” “እናንተ የባፕቲሰት አገልጋዮች፡ ይህ ሰው የደቡብ ባፕቲሰት ኮንቬንሽን ነው የላኩት ወይስ በራሱ ነው የመጣው? ” በማለት ጠየቃቸው፤ አልመለሱለትም። ሁሉንም፡ ያውቃቸዋል፦ “እየጠየቅኳችሁ ነው!” አላቸው።

253 እነርሱም መልሰው፦ “የመጣው በራሱ ነው፡” አሉ። ባፕቲሰቶች በመለኮታዊ ፈውስ እንደሚያምኑ፡ አውቃለሁና። ስለዚህ እነርሱም “በራሱ ነው የመጣው፡” ብለው መለሱለት።

254 ከዚያ በኋላ የሆነው ይህ ነው። ወንድም ቦሰዋርዝ መጣና፦ “ወንድም ብራንሃም ጉባኤው ውሰጥ እንዳለ አውቃለሁ ብሎ ተናገረ፡ መጥቶ ጉባኤውን ቢያሰናብትልን፡ መልካም ይሆናል አለ።”

ሆዋርድም አለ፦ “ታግሰሃል!”

እኔም “ታግሼአለህ፡” አልኩ።

255 ወድያው የሆነ ነገር መጣና፡ ዙርያዬን መዞር ጀመረ፡ የጌታ መልአክ እንደሆነም አወቅኩት “ተነሣ!” አለኝ፤

256 እኔ ወደ መድረኩ እሰክደርሰ ድረሰ፡ አምሰት መቶ የሚያህሉ ሰዎች፡ እጆቻቸውን **እንዲህ** አርገው መተላለፍያ አረጉልኝ።

257 እኔም “ወዳጆች ሆይ፡ እኔ መለኮታዊ ፈዋሽ አይደለሁም። እኔ ወንድማችሁ ነኝ፡” አልኳቸው። “ወንድም ቤሰት፡ ያለ እንዳች... ” ወይም፡ “ወንድም ቤሰት፡” እኔ አልኩት፦ “ወንድሜ በጭራሽ፡ አንተን ዝቅ ማድረጌ አይደለም፡ አልኩት። ሰለ አመለካከትህ ሙሉ መብት አለህ፡ እኔም እንደዛው።” እንዲ አልኩት፦ “ምንም እንኳን፡ በወንድም ቦሰዋርዝ የቀረበልህን፡ ነጥብ፡ መልሰ መሰጠት ባትችልም። የሱ ብቻ አይደለም፡ እነዚህ ነገሮች ከመጽሐፍ ቅዱሰ የተረዳ ሰው ቢሆን አትችለውም።” አልኩትም፦ “ሰዎችን ሰለመፈወሰ ከሆነ፡ ወንድም ቤሰት ሆይ፡ እኔ ፈዋሽ አይደለሁም። ነገር ግን ጌታ ሲፈውሰ ተአምር ማየት ከፈለግክ፡ ወደዚህ ና፡ ዘወትር ምሽት እዚህ አለሁ፡ በየምሽቱ ተአምር ያደርጋልና።”

258 እርሱም፦ “እንዱን ሰትፈውሰው ማየት እፈልጋለሁ ከዚያ በኋላ አያቸዋለሁ! ግን፡ በአሰማትህ ልታፈዝዛቸው ትችላለህ” አለኝ፤ “ከዚያ በኋላ ከአንድ አመት በኋላ አያቸዋለሁ!”

“ጥሩ፡ ወንድም ቤሰት፡ እነርሱን የመመርመር ሙሉ መብት አለህ፡” አልኩት።

259 እርሱም፦ “እናንተ የባዶ ቅል ሰብሰብ ወንበር-ሰባሪዎች ናችሁ ይሄን የምታምኑት። እኛ ባፕቲሰቶች እንዲህ አይነቱ ትርጉም አልባ ነገር አናምንም አለ።”

260 ወንድም ቦሰዋርዝም “ቆይ አንዴ፡” አለና። እሰኪ አላቸው፡- “ባለፉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ በነበሩ ጉባኤዎች፡ በዚህ በሂዩስተን ከሚገኙ፡ የባፕቲስት አብያተ ክርስትያናት አባላት የሆናችሁ ወንድም ብራንሃም፡ እዚህ በቆየባቸው ቀናት ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ እንደፈወሳችሁ ያረጋገጣችሁ ስንቶች አላችሁ? ” ከሶሶት መቶ በላይ የሚያህሉ ሰዎች ተነሱ። “አሁንስ ምን ትላለህ? ” አለው፤

261 እርሱም፡- “እነዚህ ባፕቲስቶች አይደሉም አለ!” እንዲሁም፡- “ማንም ሰው የፈለገውን ነገር መመሰከር ይችላል፡ ምስክርነቱ ትክክል አያሰደርገውም!”

262 እኔም አልኩት፡- “የእግዚአብሄር ቃል ትክክል እንደሆነ መሰክሯል፡ ይሄን መመለስ አትችልም። ህዝቡም ትክክል ነው ብለዋል፡ ይሄን ማንቋሸሽ አትችልም። ስለዚህ ከዚህ በላይ ምን ለማለት ፈለግክ? ” አየህ፡ በቃ።

263 እኔ ልንገርህ፡- “ወንድም ቤሰት፡ እውነት ብቻ ተናግሬአለሁ። እውነተኛ ከሆንኩ፡ ጌታ የእኔን እውነት ማረጋገጥ ግዴታ አለበት።” “ካልሆነ ግን… እውነትን ማረጋገጥ ካልቻለ፡ ጌታ አይደለም፡” አልኩት። “እኔ ሰዎችን አልፈውሰም። ነገሮች ሲሆኑ እና ሲፈጸሙ፡ የማየት ሰጦታ ተሰጥቶኝ——የተውለድኩ ሰው ነኝ፡” አልኩት። “በተሳሳተ መንገድ እንደሚረዱኝ አውቃለሁ፣ ነገር ግን የልቤን እምነት ከማሟላት ያለፈ ምንም ማድረግ አልችልም፡” አልኳቸው። እኔ፡- “ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መነሣቱ አምናለሁ። ይህ እየመጣ ራእዮችን እና የተለያዩ ነገሮችን የሚያሳየኝ መንፈስ፡ ጥያቄ ከፈጠረባችሁ፡ ወርዳችሁ ለምኑ እና እወቁ።” “ይሄ ነው፡” አልኳቸው። ነገር ግን እላለሁ፡ “ስለራሴ ግን፡ በራሴ የማደርገው አንዳች ነገር የለኝም።” “እውነት ከተናገርኩ፡ እግዚአብሄር እኔ ስለተናገርኩት እውነት፡ እንዲመሰክር ባለ ግዴታ ነው፡” አልኳቸው።

264 ልክ እንደዚያ ባልኩበት ቅጽበት፡ “ውሽሽሽሽሽሽሽ!” እያለ ይሆን ነገር አለፈ፡ እርሱ እራሱ መጣ፡ እርሱ ወረደ። እና በሂዩሰተን፡ ቴክሳስ የሚገኘው፡ የአሜሪካ ፎቶግራፈር ማህበር የሆነውን ዳግላስ ሰቱድዮ፡ እጅግ ትልቅ ካሜራ ደቅኖ ነበርና፣ የታቀደ ካልሆነ በቀር፡ (ተራ ሰዕሎች እንዳያነሱ ቀድሞ ተነግሯቸው ነበር።)

265 የአቶ/ ቤሰት ሰዕሎችን ለማንሳት በተዘጋጁ ጊዜ፡ እንዲህ——አላቸው፡ ወደዚያ እሰከምሄድ ድረስ፡ “ትንሽ ጠብቁኝ! የሚወጡ ሰድሰት ወፋፍራም መጽሔቶች አሉኝ!” አላቸው፡ “ከዚያ፡ አሁን አንሡኝ!” አላቸው፤ እንዲህ አርጎ፡ ጣቱን በቅዱሱ ሰው በሽማግሌው አፍንጫ ላይ እየጠቆመ፡- “አሁን አንሡኝ አላቸው!” እነርሱም አነሡት። ከዚያ በኋላ እንደሚማታ ሰው እጆቹን ጨብጦ አነሳ፡ እና፡- “አሁን አንሡ!” እነርሱም በዚያ መልክ አነሱት። ምስሉን ለመቅረጽ፡ እንደዚያ አደረገ። እንዲህ አርጎ፡- “ይህንን በመጽሔቴ ውሰጥ ታየዋለህ!” አለው።

266 ወንድም ቦሰዋርዝ ምንም ሳይናገር ባለበት ቆሞ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን የዚህኛው ፎቶ ምስል አነሱ።

267 (ያነሳው ልጅ ካቶሊክ ነበር)፣ የዚያኑ ቀን ማታ ላይ ወደ ቤት ሲመለሱ፣ ለሌላ ጓደኛው፡ “ስለዚህ ነገር ምን ታሰባለህ? ” ብሎ ይጠይቀዋል፤

268 “እንደተቸሁት አውቄአለሁ። እንቅርት የነበራት ሴት ጉሮሮዋን ሲለቃት፡ በአስማት አፍዝዟት ነው ብየ ነበር፡” አለው። “ምናልባት ሳልሳሳት አልቀርም፡” አለው።

“ስለዚያች ስዕል ምን ታስባለህ? ” ብሎ ጠየቀው፤

“እንጃ እኔ አላውቅም።”

269 አሲድ ውስጥ አጠቡት። ፎቶው እዩት ይሄውና፡ ከፈለጋችሁ እርሱን ጠይቁት። ወደ ቤት ሄዱ፡ ቁጭ አለና ሲጋራውን አጨሰ። ወደ ውስጥ ገብቶ የወንድም ቦሰዎርዝ የመጀመርያውን ስዕል አወጣ፡ ተቃጠለ። ሁለተኛውን ሳበ፣ ሦስተኛ፣ አራተኛ፣ አምስተኛ፣ ስድስተኛውን ሳበ ሁሉም ተቃጥለዋል። እግዚአብሄር በዚያ ስፍራ የቆመለትን የቅዱስ ሰው ምስሎች እንዲወጣ አልወደደም ግብዙ ሰው፡ እጆቹን፡ አፍንጫው ላይ ቀሰሮበት፡ አፍንጫውን ለመምታት እጆቹን ጨብጦበት እንዲነሳ አልፈቀደም። እንዲወጣ አልወደደም።

270 ቀጣይ ምስል በሳቡት ጊዜ፡ እነሆ ወጣ። እነርሱ እንዳሉት፡ ሰውየው፡ በዚያን ምሽት ልቡ ካደው።

271 የምስሉን ፊልም ወደ ዋሺንተን፡ ዲሲ ላኩት። የባለቤትነት መብት ተጠብቆለት፡ ተመለሰ።

272 ጆርጅ ጄ. ላሲ፡ የተባለ የኤፍ.ቢ.አይ. የጣት አሻራ እና ምዝገባዎች ሐላፊ፡ የነበረውን ሰው፡ እርሱም በመላ ዓለም ከሚገኙ ባለሞያዎች ዋና የሆነው ሰው ጋር፡ አመጡት እና ካሜራውን፣ ብርንሃኖችን፣ ወዘተ እንዲመረምር ሁለት ቀናት ያህል ከእርሱ ጋር ቆየ። ከከሰዓት በመጣን ጊዜ፡ እንዲህ አለኝ፦ “ሬቨረንድ ብራንሃም፡ እኔም፡ የአንተ ተቃዋሚ ነበርኩ።” “እነዚህን ብርሃናት ወዘተረፈ እየሁ ብሎ ማንም ሰው ሲናገር፡ ሳይኮሎጂ ነው እል ነበር፡” አለኝ። አክሎም እንዲህ አለ፦ “ታውቃለህ፡ የድሮው ግብዞች እንዲህ ይሉ ነበር።” (የማያምን ማለቱ ነው) “‘በክርስቶስ ራስ ላይ፡ በቅዱሳን ላይ፡ የሚታየው ጸዳል የምታውቋቸው ስዕሎች ሁሉ፡’ እነርሱ፦ ‘ተራ ሳይኮሎጂዎች ነበሩ።’” ነገር ግን፦ “ሬቨረንድ ብራንሃም፡ የዚህን ካሜራ ሜካኒካል አይን ግን ሳይኮሎጂን እያነሣም! ሌንሱ ጸዳሉን አነስቷል፡ ወይም ኔጋቲቩን አነሰቶታል፡ በዚያም የነበረ ነው።” ሲናገርም...

273 ለእነርሱ ሰጥቻቸዋለሁ። “ኦህ፡ ጌታዬ፡ ዋጋው ምን ያህል እንደሆን ያውቃሉ? ” አለኝ፤

እኔም “ለእኔ አይደለም፡ ወንድሜ፡ ለእኔ አይደለም፡” አልኩት። እርሱም ተናገረ...

274 “አዎን፡ አንተ በህይወት እስካለህ ትርጉሙ አይታወቅም፡ አንድ ቀን ግን፡ ሰልጣኔ ከቀጠለ፡ ክርስትናም ከኖረ፡ በዚህ ላይ የሚሆን ነገር አለ።”

275 ስለዚህ፡ ወዳጆቼ ሆይ፡ ዛሬ ምሽት፡ ምናልባት በምድር የመጨረሻችን ጉባኤ ከሆነ፡ እናንተ እና እኔ በልዑል አምላክ ፊት አለን። ምስክርነቴ እውነት ነው። ይሄን ለመጻፍ፡ እጅግ ብዙ፡ ብዙ የመጽሐፍ ቅጂዎች ይጠይቃል፡ እኔ ግን እንድታውቁት እፈልጋሉ።

276 እስኪ እዚህ ካላችሁ ሰዎች መካከል፡ እኔ እየሰበክኩ ስዕሉ ላይ ያለውን ሳይሆን፡ ያንን ብርሃን በአካል ያያችሁ ሰንቶች አላችሁ? በህንጻው ሁሉ ያላችሁ፡ አይታችሁት የምታውቁ፡ እጃችሁን አንሡ። አያችሁ፡ እዚህ ከተቀመጡት ሰምንት ወይም አሰር ሰዎች አሉ።

277 ምናልባት እናንተ፡ "እነርሱ—አይተዉት እኔ ላላየው እችላለሁ ካላችሁኝ? " አዎን፡ ይቻላል።

278 ሰብአ ሰገል ሲከተሉት የነበረ—ኮከብ፡ ጉበኞችን ሁሉ አልፎአል። ከእነርሱ በቀር ግን ያየው ሰው አልነበረም። ያዩት ብቸኞች ሰዎች እነርሱ ብቻ ናቸው።

279 ኤልያስ የእሳት ሰረገሎችን እና እሳትን ሁሉ፡ እና ሌሎችን ነገሮች እያየ ቆሞ ነበረ። ጊያዝ ግን ዙርያውን እያየ፡ እነርሱን ማየት አልቻለም ነበር። ጌታ ሆይ "ያይ ዘንድ አይኖቹን ክፈት፡" አለ። ከዚያ በኋላ አያቸው፡ ገባችሁ። ብርቱ ወጣት ነው፡ ዙርያውን ለመቃኘት ቆሞ ነበር፡ ሊያያቸው ግን አልተቻለውም። አዎን። ጥቂቶች እንዲያዩ ይሰጣቸዋል፡ ጥቂቶች ግን አይሰጣቸውም። ይህም እውነት ነው።

280 አሁን ግን እናንተ ፈማችሁ ያላያችሁ፡ ፈጽማችሁ አላያችሁትም፡ እናንተ በተፈጥሮ አይኖቻችሁ ያያችሁት ነገር ግን በሰዕሉ ያላያችሁት፡ ከእናንተ በተፈጥሮ አይናችሁ ካያችሁት ይልቅ በሰዕሉ ያዩት ሰዎች የበለጠ ማሰረጃ አላቸው። ምክንያቱ እናንተ፡ ያያችሁት በተፈጥሮ አይኖቻችሁ ነው፡ ልትሳሳቱም ትችላላችሁ፡ ኦፕቲካል ቅዠት ሊሆንም ይችላልና። ትክክል ነው? ይሄኛው ግን ኦፕቲካል ቅዠት አይደለም፡ እውነታ ነው፡ የሳይንስ ተመራማሪዎች ሳይቀር አረጋግጠውታል። ስለዚህ ይህን ያደረገው እራሱ ጌታ ኢየሱስ ነው።

"ወንድም ብራንሃም ሆይ፡" "ይህ ነገር ምንድነው ትላለህ? " ብላችሁ ብትጠይቁኝ፤

281 የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ወደ ፍልስጤም የመራቸው ያው የእሳት ዓምድ ነው ብዬ እምናለሁ። በእሰር ወደ ነበረው—ወደ ቅዱስ ጴጥሮስ መጥቶ ጎኑን የነካው ከዚያም ወደፊት ሄዶ በሩን የከፈተ፡ ወደ ብርሃንም የመራው ያው የብርሃን መልአክ እንደሆነ እምናለሁ። እንዲሁም እርሱ ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው ይሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ እንደሆነ እምናለሁ። አሜን! ትላንትና የነበረው እርሱ ኢየሱስ ዛሬም እርሱ ነው። ለዘለአለምም ያው ኢየሱስ ሆኖ ይኖራል።

282 ስለሱ በምናገርበት ቅጽበት አሁን፡ በምስሉ ላይ የሚታየው ያው ብርሃን... አሁን እኔ ከቆምኩበት ሁለት ጫማ የማይሞላ ርቀት ቆሟል። ይህ እውነት ነው። በገዛ—አይኖቼ አላየውም፡ እዚህ ቆሞ እንዳለ ግን አውቃለሁ። አሁን በውስጤ እየገባ ንዳለ ይታወቀኛል። አቤት! የልዑል አምላክ ኃይል ሲይዛችሁ ያለውን ልዩነት፡ እና ነገሮች እንዴት በተለየ መልኩ እንደሚታዩ ብቻ ማወቅ በቻላችሁ!

283 ለሁላችሁ፡ የቤት ስራ ነው። ለታመሙት የመጸለይ ሐሳብ አልነበረኝም፡ እኔ የምለውን ላሰብላችሁ ነበር። ራዕዮች ግን ህዝቡ ራስ ላይ ተገልጠዋል። ኦህ-አቤት። እግዚአብሄር ያውቀዋል። የጸሎት መሰመር አልጠራም፡ ባላችሁበት

እዚያ እንድትቀመጡ እተዋችኋለሁ። የጸሎት ካርድ የሌላችሁ ስንቶች ናችሁ? የጸሎት ካርድ የሌላችሁ፣ የጸሎት ካርድ የሌላችሁ ሰዎች፣ እጆቻችሁን አሳዩን።

284 እዚህ ጋር ቁጭ ያልሽ ጥቁር ሴት፡ እጅሽን ወደ ላይ እንዳወጣሽ አይቻለሁ። ልክ ነው? እስኪ ቆም በዪ በአንቺ ልጀምር። መንፈስ ቅዱስ የሚናገርሽ ገና አላወቅኩም፡ አንቺ ግን በቅንነት እኔን እየጠበቅሽ ነሽ። የጸሎት ካርድም የለሽም። ችግርሽ ምን እንደሆነ ልዑል እግዚአብሄር ቢገልጽልኝ... ለመጀመር ያክል ብቻ ነው፡ ለመጀመር ነው ይሄን የማደርገው። ታምኚኛለሽ... እኔ አንዳችም ነገር... ምንም መልካም የሌለኝ ሰው ነኝ። ምናልባት ባለ ትዳር ከሆንሽ፡ ከባልሽ የበለጠ ነገር የሌለው ሰው ነኝ። ሰው ብቻ ነኝ። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ ግን፡ እነዚህን ነገሮችን ለመግለጥ መንፈሱን ልኳል።

285 (መቼም በምንም መልኩ ከአንቺ ጋር ዝምድና እንደሌለኝ ታውቂያለሽ) እግዚአብሄር ችግርሽን ከገለጸልኝ፡ በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? [ያቺ እህት ተናገረች—እርታዒ።] ጌታ ይባርክሽ። እንግዲያውስ ከፍተኛ የደም ግፊት ለቆሽ ሄዷል። የነበረብሽ ይህ ነው። ትክክል አይደለም? ቁጭ በዪ እሺ።

286 ብቻ አንዴ እመኑ! እንድታምኑት ለሁላችሁ የቤት ስራ እሰጣለሁ።

287 ተመለከቱ፡ አንድ ነገር ልንገራችሁ። ማርታ፡ ጌታ ኢየሱስ ወዳለበት መጣች። ምን ማድረግ እንዳለበት እብ ካሳየው በኋላም... ጸጋው ላይሰራ ይችል ነበር። ላይሰራ ይችል ነበር። እሷ ግን፡- “ጌታ ሆይ፡ አንተ... በዚህ በሆንህ ኖሮ፡ ወንድሜ ባልሞተም ነበር።” አሁንም ግን “ከእግዚአብሄር የምትሻውን ሁሉ፡ እግዚአብሄር ለአንተ ያደርግልሃል፡” አለችው።

288 እርሱም፡- “ትንሣኤና ህይወት እኔ ነኝ፡ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ፡ ህያው ይሆናል። ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን አላት? ”

289 እሷ የመለሰችለትን መልስ አድምጡ። እንዲህ አለችው፡- “እምናለሁ፡ ጌታ ሆይ። አንተ ያልከው ሁሉ እውነት እንደሆነ አምናለሁ። ወደ ዓለም የሚመጣው የእግዚአብሄር ልጅ አንተ እንደሆንክ እኔ አምናለሁ።” አቀራረቧ፡ በትሕትና ይህ ነበር።

ህመምሽ ጠፋ፡ አይደልም’ዴ፡ እመቤት? አዎን። ትክክል።

290 ከጎንሽ፡ የተቀመጠች ወጣት እመቤትም፡ በሴቶች ችግር፡ እና በአርቲራይትስ ህመም ትሰቃያለች። ትክክል አይደለም፡ እመቤት? ቀይ ቀሚስ የለበሰሽው ሴት፡ ለአንድ ደቂቃ ብቻ ቁሚ። ተጠግተሽ ስለነበርሽ፡ ራዕዩ ወደ አንቺ መምጣት ነበረበት። እርቲራይትስ፣ የሴቶች ችግር። ትክክል ነው? በህይወትሽ ያለ ሌላ ነገርም ይህ ነው (በደንብ ስትታዩ ይህ ነገር—አለብሽ)፤ በህይወትሽ ብዙ ጭንቀት፣ ብዙ ችግር አለ። ችግሩ በቤተሰብሽ ውስጥ ነው፡ ባለቤትሽ ነው። ሰካራም ነው። ወደ ቤተክርስትያን አይሄድም፡ እውነት ከሆነ እጅሽን አንሺ። ጌታ ይባርክሽ፡ እመቤት። በረከትሽን ተቀብለሽ ወደ ቤትሽ ሂጂ። ተፈውሰሻል፡ ብርሃን በላዪሽ በርቷል።

291 አንተኛው በአጠገቡ የተቀመጥከው ሰው። አንተኛው፡ ወዳጄ፡ ታምናለህ? [ያ ወንድም፡- “አዎን እምናለሁ፡ አለ።”—እርታዒ።] በሙሉ ልብህ? [“አዎን፡

ጌታዬ።] ከስሜት ህዋሶችህ አንደኛው ተጎድቶብሃል። የማሽተት ስሜትህ ነው። እውነት አይደለም? ከሆነ፡ እጅህን አወዛውዝ። ["በጣም ጥሩ።"] እጅህን **እንደዚህ** አፍህ ላይ፡ አድርግ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በሙሉ ልቤ አምንሃለሁ፡" በል። ["ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በሙሉ ልቤ አምንሃለሁ።"] ጌታ ይባርክህ። መሄድ ትችላለህ። ፈውስህን ትቀበላለህ።

292 በእግዚአብሔር ላይ እምነት ይኑራችሁ! ከኋላ ያላችሁ፡ ሁላችሁም ስለሱ ምን ትላላችሁ? አምናችኋል? ትሁት ሁኑ!

293 እዚያ ጥግ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣለች። ያ ብርሃን በእሷ ላይ አብርቶባት አያለሁ። ስለ እሱ መናገር የምችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው፡ ብርሃኑ ሲያበራ። **እዚህ** ያለው ብርሃን በሴትየዋ ላይ አብርቷል። ምን እንደሆነ ለማየት፡ ምናልባት ጥቂት ደቂቃዎች። ከዚያ ይገልጠዋል... ሴቲቱ በልብ—ህመም እየተሰቃየች ናት። እኔን ታየኛለች።

294 ባለቤትዋም ከጎኗ ተቀምጧል። ባለቤትዋም ትንሽ ህመም አለበት፡ ታሞ ቆይቷል፡ ቁርጠት፡ ህመም። ልክ አይደለም፡ ወዳጄ? እውነት ከሆነ እጅህን አንሣ። እውነት ነው፡ ትንሽ ሰካርፍ ያደረግሽው፡ እመቤት፡ አንቺ ነሽ። ጋሼ፡ እውነት አይደለም? ዛሬ ቁርጠት አልነበረብህም? ሰውየው፡ የሆድ ቁርጠት አሞህ ነበር። ትክክል።

295 ሁላችሁ ሁለታችሁ፡ ከልባችሁ ታምናላችሁ? ተቀብላችኋል? ወዳጄ፡ ደግሜ፡ ልንገርህ፡ እጆችህ ከፍ ብለው አያለሁ፡ የማጨስ ሱስ አለብህ። አቁም። ሲጃራን ታጨሳለህ፡ ማጨስ የለብህም፡ ህመምተኛ ያደርግሃል። ትክክል አይደለም? ትክክል ከሆነ፡ እጆችህን አወዛውዝ። ቁርጠቱ ከዚያ የመነጨ ነው። ነርቮችህ ላይ ጫና ያደርጋል። ክፉ ነገሮችን አስወግድ ከአሁን በኋላ አትጠቀም፡ ከዚያ በኋላ ታሸንፈዋለህ ጤነኛም ትሆናለህ፡ ሚስትህም የልብ ህመም ይተዋታል። ታምናለህ? ትክክል አይደለም? ከዚህ ሆኜ አላይህም፡ አንተም ታውቀዋለህ፡ ነገር ግን አሁንም ከ—ከፊት ኪስህ ውስጥ... ሲጋራ ይዘሃል። ትክክል። እነዚያን ነገሮች አውጣና እጅህን በሚስትህ ላይ አኑር፡ ከአሁን በኋላ ከእንደዚህ አይነት ነገር እንደምትርቅ ለጌታ ቃል ግባለት፡ ድነህ ቤት ትሄዳለህ፡ አንተ እና ሚስትህ ትፈወሳላችሁ። የጌታ ኢየሱስ ስም የተባረከ ይሁን!

በሙሉ ልብ አምነሃል?

296 ይህች ወጣቷ እመቤት እዚህ ተቀምጣ እያየችኝ ነው። አንቺ... እዚህ የፊት ወንበር ላይ፡ ተቀምጠሽ ያለሽው። እኔን እያየሽ፡ እዚያ ጋር የተቀመጥሽው... ወጣት እመቤት። እዚጋ፡ ያለሽው እመቤት፡ የጸሎት ካርድ ይዘሻል... አልያዝሽም? ምንም የጸሎት ካርድ የለሽም? በሙሉ ልብሽ ታምኛለሽ? ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያድንሽ እንደሚችል ታምኛለሽ?

297 ከእሷ አጠገብ ተቀምጠሽ ያለሽው እመቤት፡ ምን ይመስልሻል? የጸሎት ካርድ አለሽ፡ እመቤት? የለሽም? አንቺስ ደህና መሆን ትፈልጊያለሽ? የሆድ ህመም ከመታመምሽ በፊት እንደበፊቱ እንደገና መብላት አላማረሽም? ኢየሱስ እንደፈወሰሽ ታምኛለሽ አሁን? ኢየሱስ ክርስቶስ እንድፈወስሽ ካመንሽ ቁሚ። ጨጓራሽ አልሰር ህመም ነበረበት፡ አይደልም'ዴ? ከመበሳጨት የተነሳ ነው። ለብዙ አመታት ብስጩ ነሽ። አሲዶች እና ሌሎችችን ይፈጥራሉ፡ በተለይ

ደግሞ አሲድ፣ ምግብ አፍሽ ውስጥ ስታስገቢ ጥርሶችሽን ስሜቱ ከባድ ያደርግብሻል። እውነት ነው። አዎን፡ ወዳጄ። በጨጓራሽ ውስጥ የተዘረጋ፡ ፔፕቲክ አልሰር ነው። አንዳንዴ ያቃጥልሻል በተለይ ደግሞ ቶሰት በገበታ ቅቤ ስትበዪ። ልክ ነው? እእምሮሽን እያነበብኩ አይደለም፣ መንፈስ ቅዱስ ግን የማይሳሳት ነው። አሁን ተፈውሰሻል። ወደ ቤትሽ ሂጂ፣ ደህና ሁኚ።

298 በዚህ አቅጣጫ ያላችሁ ሰዎችስ ምን ታስባላችሁ? በዚያ በኩል ያላችሁ አንዳንዶች የጸሎት ካርድ ያልደረሳችሁ፡ እጆቻችሁን አንሡ። የጸሎት ካርድ ያልደረሰው አንድ ሰው። መልካም፡ ትሁታን ሁኑ፡ በሙሉ ልባችሁ እመኑ። በረንዳው ላይ ያላችሁ ሰዎችስ? በእግዚአብሄር እመኑ።

299 ከሉአላዊ ጸጋው የተነሣ እንጂ፡ እኔ በራሴ ይሄን ማድረግ አይቻለኝም። ታምናላችሁ? እኔ መናገር የምችለው እርሱ በሚያሳየኝ ልክ ነው። እንደየእምነታችሁ... እኔ ይሄን የምናገረው ከእምነታችሁ ጋር ለመገናኘት ነው፡ ከዚያ በኋላ ወዴት እንደሚመራኝ አያለሁ። ይህ ከወንድማችሁ እንዳይደለ—ይህን ተገንዝባችኋልን? በእሱ ፊት ቆማችኋል። ይህን የሚያደርገው እኔ አይደለሁም፡ አንቀሳቃሹ እምነታችሁ ራሱ ነው። እኔ ላንቀሳቅሰው አልችልም። እምነታችሁ ነው። እኔ እሱን ማንቀሳቀስ የምችልበት መንገድ የለኝም። ቆዩ አንድ ደቂቃ።

300 በዚያ ጥግ፡ መነጽር ያደረገ፡ ጥቁር ሽማግሌ ቁጭ ብሎ ይታየኛል። የጸሎት ካርድ ይዘዋል፡ ጋሼ? እሰኪ አንዴ ይቁሙ። የእግዚአብሄር ባርያ መሆኔን፡ በሙሉ ልብ ያምኑኛል? ጭንቀትዎ ስለ ሌላ ሰው ነው፡ አይደለም'ዴ? ትክክል ከሆነ፡ እጅትን ያወዛውዙልኝ። ስለ እኔ አይደለም፡ ወንድምዎ ነኝ። አሁን፡ እርሶ የጸሎት ካርድ አልያዙም። የጸሎት ካርድ ካልያዙ ደግሞ፡ ወደ ጸሎት መሰመር የሚገቡበት ምንም መንገድ አይኖሮትም ነበር። እናንተ፡ የጸሎት ካርድ የያዛችሁ ሰዎች፡ ካላችሁበት—አትነሡ—እንዳትነሡ፡ ወደ መሰመር የምትወጡበት ዕድል አለ፡ እያችሁ።

301 እኔ ብርሃን በላዩ ላይ ሲያበራ እየዋለሁ። እስከ አሁን ድረስ ራዕይ ወደ መሆን አልተቀየረም። እኔ ልፈውሶ አይቻለኝም፡ ወንድሜ፡ እኔ አልችልም። ያን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሄር ብቻ ነው። እርሶ ግን... እምነትዎ... እርሶ እምነት አለዎት። እያመኑ ነዎት። ይህ እንዲሆን—የሚያደርግ፡ የሆነ ነገር—በሆነ መንገድ፡ የሆነ ነገር አለ።

302 ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ችግሩ ምን እንደሆነ ለዚህ ሰው ቢነግረው፣ ሌሎቻችሁ ፈውሳችሁን ትቀበላላችሁን? ከእኔ አሰር፣ አሰራ አምስት፣ ያርዶችን ርቆ የቆመ ሰው ነው፣ በህይወቴ አይቼው አላውቅም። ለእኔ እዚያ የቆመ ሰው ብቻ ነው። ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ በዚያ ሰው ላይ ያለውን ችግር ከገለጸ፣ ሁላችሁም ጤናማ ሰዎች ሆናችሁ ትሄዱ ዘንድ ይገባችኋል። እግዚአብሔር ከዚህ በላይ ምን ማድረግ ይችላል? አይደል'ዴ?

303 ጋሼ፣ አንተ ላይ ምንም ችግር የለም። ትዳከማለህ፣ ማታ ሲሆን ትነቃለህ፣ የፕሮስቴት እና አንዳንድ ችግሮች አሉብህ፡ ዋናው ችግርህ ግን እሱ አይደለም። ችግርህ የልጅህ ነው። ልጅህ በአንድ የመንግሰት ተቋም ውስጥ ገብቷል፡ እና የድርብ ሰብዕና ችግር አለበት። ልክ ነው? ትክክል ከሆነ እጅዎን ያወዛውዙ። በትክክል ትክክል ነው።

304 አሁን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እዚህ መቆሙን ስንቶች ታምናላችሁ? ቆመን ምስጋና እናቅርብ ፈውሳችንን እንቀበል።

305 ሁሉን ቻይ አምላክ፣ የሕይወት ባለቤት፣ የመልካም ስጦታ ሁሉ ሰጪ፣ ያው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ያው ትናንት፣ ዛሬ እና ለዘላለም፡ አንተ እዚህ አለህ።

306 አሁንም፡ ሰይጣን፡ ይህን ህዝብ ለብዙ ዘመን አታለሃል፡ አሁን ዉጣ ከውስጣቸው! በመገኘቱ አሁን እዚሁ በእሳት ዓምድ አምሳል ባለው፣ በሕያው አምላክ እገስጽሃለሁ እነዚህን ሰዎች ልቀቅ! በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ልቀቃቸው!

307 እጆቻችሁን እያነሣችሁ ሁላችሁ እግዚአብሄርን አመሰግኑ፡ ሁላችሁ፡ ፈውሳችሁን ተቀበሉ።

**መልአኩ ወደ እኔ የመጣበት ምክንያት፡ እና ተልዕኮው** AMH55-0117

(How The Angel Came To Me, And His Commission)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ጥር 17፡ 1955፡ ሰኞ ማታ በዩ/ኤስ/ኤ/፡ ቺካጎ፡ ኤሊኖስ፡ ከሚገኘው ሌን ቴክ ሃይ ስኩል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

# የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org